# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅ አሞላል መመሪያ

ታህሣስ 2005
አዲስ አበባ

17

ማውጫ

ገፅ

1. መግቢያ ---------------------------------------------------------------------1
2. ማምረት/ማምረቻ ---------------------------------------------------------------1
3. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ትርጉም ---------------------------------------2
4. የጥናቱ ዓላማዎች ---------------------------------------------------------------2
5. በጥናቱ የሚሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች ---------------------------------------3
6. መጠይቁን ለመሙላት የሚያስችሉ አጠቃላይ ማብራሪያዎች -------------3
7. ክፍል 1 የአካባቢ መለያ -----------------------------------------------------6
8. ክፍል 2 ስለፋብሪካው መሠረታዊ መረጃዎች --------------------------------9
9. ክፍል 3 በ2004 ዓ.ም በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ብዛት፤ደመወዝና ምንዳ ---------------------------------------------------------------------17
10. ክፍል 4 በ2004 ዓ.ም በፋብሪካው የተመረቱና የተሸጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ---------------------------------------------------------------22
11. ክፍል 5 በ2004 ዓ.ም የተከማቹ ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ፤የጥሬ ዕቃ ግዢና የምርት መጠን ---------------------------------------------------------26
12. ክፍል 6 በ2004 ዓ.ም ፋብሪካው የተጠቀመባቸው ጥሬ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች -----------------------------------------------------------28
13. ክፍል 7 የቋሚ ንብረትና የመዋዕለ ንዋይ ወጪ ----------------------------34
14. ክፍል 8 በ2004 ዓ.ም ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ስላለመስራቱና ያጋጠሙ ልዩ ልዩ ችግሮች ----------------------------------------------------43
15. ክፍል 9 የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ICT አጠቃቀም ቅጽ አሞላል መመሪያ------------------------------------------------------------47
16. ክፍል 10 አስተያየት ---------------------------------------------------------51
17. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ዓመታዊ ጥናት የተሞሉ መጠይቆች የማመሳከሪያ ዘዴዎች ---------------------------------------52
18. የቋሚ ንብረት አገልግሎት ቅናሽ ማባዣ ---------------------------------56
19. የምርት ዓይነትና የመጠን መለኪያ ዝርዝር--------------------------------57
20. የጥሬ ዕቃ ዓይነትና የመጠን መለኪያ ዝርዝር-----------------------------64

# የ2004 ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች

# ጥናት የመጠይቅ አሞላል መመሪያ

## 1. መግቢያ፣

ወቅታዊና አስተማማኝ ስታቲስቲካዊ መረጃ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች መኖር የአንድን አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ፣ ዕቅድ ለማውጣት፣ ተግባራዊነቱንም ለመቆጣጠርና እያንዳንዱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ለሀገር ሀብት ውጤት ያለውን ድርሻ ለመከታተል አስፈላጊነቱ እሙን ነው::

ከላይ የቀረበውን አጠቃላይ ዓላማ መሠረት በማድረግ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ከማምረቻ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ውስጥ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን በየዓመቱ በማጥናት ዝርዝር ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች በማሠራጨት ላይ ይገኛል:: ይህንን የኢኮኖሚ ዘርፍ አስመልክቶ የ2004 በጀት ዓመትንም መረጃዎች ለማሰባሰብ ዕቅድ ተይዟል::

በዚሁም መሠረት ይህ የአሞላል መመሪያ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች መጠይቅን ለመሙላት እንዲያስችል ሆኖ የቀረበ ሲሆን በውስጡም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪን ትርጉም (መመዘኛ)፣ የጥናቱን ዓላማዎች፣ ጥናቱ የሚመለከተውን ጊዜ፣ የሚሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች፣ የመረጃው ምንጭ፣ የመረጃውን ሚስጢራዊነት፣ ቁጥሮች እንዴት እንደሚሞሉና ዓምድ በዓምድ በዝርዝር መረጃዎች እንዴት እንደሚጠየቁና እንደሚሞሉ ማብራሪያ ይዟል::

**2. ማምረት (ማምረቻ)**:- የጥሬ ዕቃዎችን ወይም የመገጣጠሚያዎችን ቅርጽ ወይም/እና ይዘት መካኒካዊ ወይም ኬሚካላዊ የሆነ ዘዴ በመጠቀም ወደ አዲስ ውጤት የመለወጥና የአካል መገጣጠም ሥራዎችን የማከናወን ተግባር ነው:: ከዚህ በተጨማሪም የደንበኞችን ጥሬ ዕቃ በመጠቀም የማምረት አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ወፍጮ ቤት፣ ልብስ ስፌት፣ የተለያዩ ቅርጽ ማውጣት፣ የብረታ ብረት፣ የእንጨት ውጤቶችንና የመሳሰሉትን ሥራዎች የሚያከናውኑ እንደ ማምረት ሥራ ይቆጠራሉ::

## 3. የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ትርጉም፣

የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ የሚባለው በአማካይ አሥርና በላይ ሠራተኞችን የሚያሰማራ፣ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፣ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርት ፋብሪካን ሁሉ የሚያካትት ነው:: ለምሣሌ፦ እንደ ዳቦ መጋገሪያ፣ እንጨት መሰንጠቂያ፣ የዱቄት ማምረቻ፣ የጫማ ማምረቻ፣ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካና እነዚህን የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ የማምረትና የንግድ ወይም የአገልግሎት ተግባራት በጣምራ ሊካሄዱ ይችላሉ:: በዚህ ወቅት ሁለቱም ተግባራት በሰፊው የሚካሄዱ ከሆንና የሁለቱ ተግባራት ሂሣብ ተለይቶ የሚታወቅ ከሆነ የማምረቻ ተግባሩን የሚመለከት መረጃ ብቻ ለይቶ በመጠየቅ መጠይቁን መሙላት ያስፈልጋል:: ነገር ግን የማምረቻ ድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ ከሌሎች ዘርፎች ለመለየት ካልተቻለና በአብዛኛው ድርጅቱ የተሰማራው በማምረት ተግባር ላይ ሆኖ የንግድ ወይም የአገልግሎት ዘርፍ ሥራው በተቀጽላነት የሚከናወን ከሆነ ወይም ድርጅቱ አብዛኛውን ገቢ የሚያገኘው ከማምረት ተግባሩ ከሆነ፣ የዚህ ድርጅት የሥራ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ በጥናቱ ሊካተት ይገባል:: ለምሳሌ የዚህ ዓይነትን የ ተግባር በጣምራ የያዙ ዳቦ ቤቶችና ሻይ ቤቶች በብዛት ያጋጥማሉ::

## 4. የጥናቱ ዓላማዎች፣

4.1 የዘርፉን ዕድገት በሚመለከት የኢኮኖሚ ፖሊሲና የልማት ዕቅድ አውጭዎች እንዲሁም ተመራማሪዎች በመነሻነት የሚጠቀሙበት ስታቲስቲካዊ መረጃ በኢንዱስትሪ ዓይነትና በባለቤትነት ዓይነት ለማቅረብ፣

4.2 ዘርፉ ያሠማራውን የሰው ኃይልና የምርት መጠን ለማወቅና ለአገር ሀብት የሚያበረክተውን ድርሻ ለማስላት አስፈላጊ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማስገኘት፣

4.3 ዘርፉ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ከግብርናው ጋር ያለውን መስተጋብር እንዲሁም ከውጭ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በኩል ያለውን ድርሻ ለመገመት የሚያስችሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በዝርዝር መሰብሰብ፣ የዚህ ጥናት ዋና ዋና ዓላማዎች ናቸው::

## 5. <u>በጥናቱ የሚሰበሰቡ የመረጃ ዓይነቶች፣</u>

በዚህ ጥናት የሚሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የካፒታል መጠን፣ የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም፣ የሠራተኞች ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ፣ የምርት መጠንና ዋጋ፣ የጥሬ ዕቃ ፍጆታ፣ ልዩ ልዩ ከማምረት ሂደቱ ጋር የተዛመዱና ያልተዛመዱ ወጭዎች፣ የቋሚ ንብረት ሁኔታና በቋሚ ንብረት ላይ የተደረገ የመዋዕለ ንዋይ መጠንና የማምረት ችሎታ … ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው::

## 6. <u>መጠይቁን ለመሙላት የሚያስችሉ አጠቃላይ ማብራሪያዎች፣</u>

6.1 <u>የሚሰበሰቡት መረጃዎች ምንጭ</u>፣ መረጃዎች በመጠይቁ ላይ መሞላት ያለባቸው ፋብሪካው የሚገለገልባቸውን የሂሣብ መዛግብትና ልዩ ልዩ ሰነዶች መሠረት በማድረግና የቃለ መጠይቅ ዘዴን በተጨማሪ በመጠቀም ነው:: በመዝገብ ያለመኖር ምክንያት መረጃ ሰጭዎች መልሶችን ለመስጠት የሚቸገሩ ሲሆን በተቻለ መጠን የተሟሉ መረጃዎችን በግምት ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል::

6.2 ለዚህ ጥናት የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች የሥራ እንቅስቃሴ ስታቲስቲካዊ መረጃ የሚሰበሰበው <u>ከየፋብሪካው</u> ስለሆነ **ከአንድ ዓይነት ፋብሪካ በላይ ላላቸው ድርጅቶች ለእያንዳንዱ ፋብሪካ ለየብቻ አንዳንድ መጠይቅ መሞላት አለበት**:: ስለሆነም ከአንድ ፋብሪካ በላይ ያላቸው ድርጅቶች ስለ ሁሉም ፋብሪካዎች (በአንድ የኢንዱስትሪ ዓይነትና ከተማ የሚጠቃለሉ ካልሆነ በስተቀር) መረጃ በአንድነት አጠቃልለው በአንድ መጠይቅ ማስሞላት የለባቸውም:: በተመሳሳይ መንገድ አንድ የፋብሪካ ባለንብረት ሁለት የተለያዩ ፋብሪካዎች ቢኖሩትና አንደኛው ፋብሪካ ለሌላው ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ቢሆን፣ የሁለቱም ፋብሪካዎች መረጃ መሞላት ያለበት በተለያየ <u>መጠይቅ ለየብቻ</u> ነው:: <u>ለምሣሌ</u>፡- የዱቄት ፋብሪካ እና ዳቦ መጋገሪያ፣ ወዘተ::

6.3 <u>ምስጢር ስለመጠበቅ</u>፣ በመጠይቁ ላይ የሚሞላው ማናቸውም ዓይነት መረጃ የሚፈለገው ለስታቲስቲክስ ሥራ ብቻ ስለሆነ ማለትም ተጠቃሎ እንጂ በተናጠል ለመረጃ ተጠቃሚዎች ስለማይሰጥ በሚስጢር የሚያዝ ነው::

### 6.4 ጥናቱ የሚመለከተው ጊዜ

የማምረቻ ድርጅቱን በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ የአንድ ዓመት ማለትም የ2004 የምርት ዘመንን አስመልክቶ መሆን ይገባዋል:: በመሆኑም የማምረቻ/አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱን የሂሣብ መዝገብ አያያዝ ሁኔታ በመከተልና ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት በጥናቱ መሸፈን የሚገባውን ወቅት በጥንቃቄ መወሰን ይኖርበታል::

#### 6.4.1 የማምረቻ ድርጅቱ የተሟላ የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ከሆነ:

6.4.1.1 ድርጅቱ የሂሣብ መዝገቡን የሚይዘው በኢትዮጵያ በጀት ዓመት ከሆነ፣ የድርጅቱን እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ የ2004 በጀት ዓመትን በሙሉ ወይም ከሐምሌ 1/2003-ሰኔ 30/2004 ያለውን መሆን ይገባዋል::

6.4.1.2 ድርጅቱ የሂሣብ መዝገቡን የሚይዘው በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከሆነ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ የ2004 ዓ.ም በሙሉ ወይም ከመስከረም 1/2004 - ጳጉሜ 5/2004 መሆን ይገባዋል::

6.4.1.3 ድርጅቱ የሂሣብ መዝገብ የሚይዘው በአውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ከሆነ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ የ2011 በሙሉ ወይም ከJanuary 1- December 31/2011 መሆን ይኖርበታል::

#### 6.4.2 የማምረቻ ድርጅቱ የተሟላ የሂሳብ መዝገብ የማይዝ ከሆነ

የማምረቻ ድርጅቱ የተሟላ የሂሣብ መዝገብ የማይዝ ከሆነ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚመለከት የሚሰበሰበው መረጃ የ2004 የኢትዮጵያ በጀት ዓመትን በሙሉ ወይም ከሐምሌ 1/2003 - ሰኔ 30/2004 መሆን ይገባዋል::

ማሳሰቢያ: የማምረቻ ድርጅቱ በ2004 ዓ.ም ምንም ዓይነት ምርት ያላመረተ ወይም የማምረት አገልግሎት ያልሰጠ ከሆነ ከድርጅቱ መረጃ አይሰበሰብም::

### 6.5 ቁጥሮች በመጠይቁ ውስጥ እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው፣

ቁጥሮች በሚጻፉበት ጊዜ የተጠየቀውን መረጃ ለመጻፍ በተሰጠው ዓምድ ሥር ባለው ቦታ መመዝገብ ያስፈልጋል:: ለክፍልፋይ (በክፍል 4 ንዑስ ክፍል 4.1 ዓምድ 6 የአንዱ ዕቃ መካከለኛ የሽያጭ ዋጋ እንዳለ ከነክፍልፋዩ በካርድ ኮለሞቹ ከሚሞላበት በስተቀር) መጻፊያ ቦታ ስላልተሰጠ

በክፍልፋይ ደንብ መሠረት ቁጥሮችን በማጣጋት መሙላት ያስፈልጋል። ስለአጠቃላይ አመዘጋገቡ ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሣሌ ይመልከቱ።

ስምሣሌ፦ በመጠይቁ ክፍል 3 ንዑስ ክፍል 3.1 ላይ በተራ ቁጥር 6 አቀጣጫ ስተጠየቀው ጠቅላላ ለጊዜያዊ ሠራተኞች የተከፈለው ምንዳ ወይም ደመወዝ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ብር 12472.60 ቢከፈል በክፍልፋይ ደንብ መሠረት በማጣጋት ብር 12473 ይሆናል ማለት ነው። ካርድ ኮለም ላላቸው የመጠይቁ ክፍሎች ቁጥሮች በሚመዘገቡበት ጊዜ በአንድ ካርድ ኮለም ውስጥ አንድ ቁጥር ብቻ መጻፍ ይኖርበታል።

# ክፍል 1 - የአካባቢ መለያ

## 1.1 የፋብሪካው አድራሻ /ሥራው የሚካሄድበት ሥፍራ/፣

በዚህ ክፍል ከዓምድ 1-13 በተሰጡት ክፍት ቦታዎች የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት የአካባቢ መለያ መረጃ ይሞላል:: እያንዳንዱ ዓምድ የተለያዩ የአካባቢ መለያዎችና አድራሻዎች የሚሞላበት ሲሆን በዓምዶቹ ውስጥ የሚገኙ ካርድ ኮለሞች ደግሞ ኮዶች የሚሞሉባቸው ቦታዎች ናቸው::

### ዓምድ 1 - ክልል

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት ክልል ስም ይመዘገባል:: ካርድ ኮለሞቹ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ክፍት ይተዋሉ::

### ዓምድ 2 - ዞን

በዚህ ዓምድ ሥር በተሰጠው ክፍት ቦታ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት ዞን ስም ይመዘገባል:: ካርድ ኮለሞቹ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ክፍት ይተዋሉ::

### ዓምድ 3 - ወረዳ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት የወረዳ ስም ይመዘገባል:: ካርድ ኮለሞቹ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ክፍት ይተዋሉ::

### ዓምድ 4 - ከተማ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት የከተማ ስም ይመዘገባል:: ካርድ ኮለሞቹ ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ክፍት ይተዋሉ::

### ዓምድ 5 - ክፍለ ከተማ /ከፍተኛ

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት ክፍለ ከተማ/ከፍተኛ ስም/ቁጥር እንደአግባብነቱ ተጠይቆ ይመዘገባል:: በካርድ ኮለሞቹ የከፍተኛው ኮድ ይሞላል::

**ዓምድ 6 - ቀበሌ**

በዚህ ዓምድ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት የከተማ ነዋሪዎች ማህበር (ቀበሌ) ስም/ቁጥር ይሞላል:: በካርድ ኮለሞቹ የቀበሌው ቁጥር ይሞላል:: ማሳሰቢያ:- ለውጥ ለተካሄደባቸው ቀበሌዎች በዚህ ካርድ ኮለም ላይ ሊሞላ የሚገባው ቁጥር አዲሱ ሆኖ አሮጌዉ ከግርጌ በአስተያየት ይገለፅ ::

**ዓምድ 7 - የቤት ቁጥር፣** በዚህ ዓምድ ሥር የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚገኝበት የቤት ቁጥር በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይመዘገባል::

**ዓምድ 8 - የጥናቱ ዓመት፣** የጥናቱ ዓመት 2004 የተሞላበት ስለሆነ ምንም አይሞላበትም::

**ዓምድ 9 - የፋብሪካው መደብ፣** ለቢሮ ሥራ ስለሆነ ክፍት ይተዋል::

መደጋ - ዘርፍ

**ዓምድ 10 - ፋብሪካው የተመዘገበበት ሙሉ ስም/የባለቤቱ/ቶቹ) ሙሉ ስም፣**

በዚህ ዓምድ ፋብሪካው የሚታወቅበትና የተመዘገበበት ስም በተሰጠው ካርድ ኮለም ይመዘገባል:: ፋብሪካው የሚጠራበት የራሱ የሆነ ስም ከሌለውና የተመዘገበው በባለቤቱ ስም ከሆነ የባለቤቱ ስም ከድርጅቱ ዋና ሥራ ጋር ተጣምሮ ይጻፋል:: ለምሳሌ የድርጅቱ ባለቤት ስም አቶ አየለ ለማ ቢሆንና የኢንዱስትሪው ዓይነት የቢሮ ዕቃዎች ማምረት ቢሆን በዚህ ዓምድ ውስጥ የሚሞላው አየለ ለማ የቢሮ ዕቃዎች ማምረት ይሆናል::

**ዓምድ 11 የፋብሪካው ተራ ቁጥር**

በዚህ ዓምድ ውስጥ የሚገኘው ካርድ ኮለም የሚያገለግለው ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሆነ ባዶ ይተዋል::

**ዓምድ 12 - የስልክ ቁጥር**

በዚህ ዓምድ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ፋብሪካው የስልክ ቁጥር ካለው ይመዘገባል በተቻለ መጠን የቀጥታ ስልክ ቢሆን ይመረጣል::

**ዓምድ 13 - የፖስታ አድራሻ**

በዚህ ዓምድ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ፋብሪካው የፖ.ሣ.ቁጥር ካለው ይመዘገባል::

## ዓምድ 14 - የመብራት አገልግሎት ቁጥር

በዚህ ዓምድ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን የተሰጠው ባለ 7 አሀዝ የመብራት አገልግሎት ቁጥር ይሞላል::

### 1.2 የፋብሪካው ዋና መ/ቤት ከፋብሪካው የተለየ ከሆነ አድራሻው፣

የፋብሪካው ዋና መ/ቤት ፋብሪካው ካለበት ሥፍራ የተለየ ከሆነ ዋና መ/ቤቱ የሚገኝበት ዝርዝር አድራሻ ማለትም ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ከተማ፣ ከፍተኛ/ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ፣ የቤት ቁጥር፣ የስልክ ቁጥር፣ የፖ.ሣ.ቁጥር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች በ1.1 ላይ በቀረበው ማብራሪያ መሠረት ይመዘገባሉ::

ዓምድ 15 - የጄ.ር. ኤሌክትሪሲቲ

ይህ መረጃ የሚሞላው የማምረቻ ድርጅት የሚገኝበትን የጄ.ር ኤሌ ሪሲቲ ገለ ን አካል መረጃ ይሠበሠባል

3023 [illegible]3 000

1457964

## ክፍል 2 - ስለፋብሪካው መሠረታዊ መረጃዎች

### 2.1 ፋብሪካው የሚያመርተው ምርት ምንድን ነው?

ፋብሪካው አንድ ዓይነት ምርት የሚያመርት ከሆነ የምርቱን ዓይነት ከአንድ በላይ ምርት የሚያመርት ከሆነ **ከፍተኛ ገቢ ከሚያስገኙት የምርት ዓይነቶች** በመጀመር እንደ ቅደም ተከተላቸው ሦስት የፋብሪካው ዋና ዋና የምርት ዓይነቶች በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባሉ::

ድርጅቱ የተሠማራው በትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ሆኖ የንግድ ወይም የአገልግሎት ሥራ በጣምራነት የሚያከናውን ከሆነ በዚህ ቦታ ላይ መሞላት ያለበት የማምረት እንቅስቃሴው ብቻ ነው:: ይህ መረጃ በሚሞላበት ጊዜ ዝርዝርና ግልጽ ሆኖ (በተለይ ከእንጨትና ከብረት ለሚሠሩት የቤት መሣሪያዎች ምርቱ ከምን እንደተሠራ ከጥሬ ዕቃው ዓይነት ጋር መገለጽ አለበት) በቢሮ ውስጥ ተገቢውን የኢንዱስትሪ ኮድ ለመሙላት አሻሚ በማይሆንበት መንገድ በጥንቃቄ መመዝገብ ይኖርበታል:: ስምሣሌ፦ ዳቦ መጋገር፣ ዘይት ማምረት ሣሙና ማምረት፣ ልብስ መሥፋት፣ ዱቄት ማምረት፣ የጫማ ምርት፣ የፕላስቲክ ምርት፣ እንጨት መሠንጠቅና መላግ፣ ከእንጨት ወይም ከብረት የተሠሩ የቤት መሣሪያዎችን ማምረት (በሮች፣ መስኮቶች፣ መቃኖች፣ ሞራሌዎችን ...ወዘተ ለሚያመርቱ)፣ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ማምረት፣ የሕትመት ሥራዎች፣ የሹራብ ሥራ ...ወዘተ እየተባለ መገለጽ ይኖርበታል::

### 2.2 ፋብሪካው ሌሎች ቅርንጫፍ ማምረቻዎች ካሉት ብዛታቸው ስንት ነው?

ይህ መረጃ የሚሞላለት **ፋብሪካ በሚገኝበት ከተማ ሌሎች ተመሣሣይ ምርት የሚያመርቱ ቅርንጫፍ ማምረቻዎች ካሉት ብዛታቸው ስንት እንደሆነ ተጠይቆ በተሰጠው ካርድ ኮለም ይመዘገባል**:: ይህ ማለት ፋብሪካው አንድ ዓይነት ምርት የሚያመርቱ ከአንድ በላይ ፋብሪካዎች በአንድ ክልል፣ ዞንና ከተማ ቢኖሩት ቀሪዎቹ አድራሻዎች ከፍተኛው፣ ቀበሌው፣ የቤት ቁጥሩ፣ የስልክ ቁጥሩና የፖ.ሣ.ቁጥሩ ቢለያዩም የሁሉም መረጃ በአንድ መጠይቅ ተሞልቶ የቅርንጫፎቹ(**መረጃው የሚገኝበትን ፋብሪካ ሳይጨምር**) ብዛት በዚህ ዓምድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ይሠፍራል:: የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርቱ ከሆነ ግን በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው የግድ በተለያዩ መጠይቆች መሞላት ይኖርባቸዋል::

ለምሣሌ፣ አንድ የዳቦ ቤት ባለቤት በአንድ ከተማ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ሁለት የዳቦ ማምረቻና አንድ ዱቄት ፋብሪካ ቢኖረው ለሁለቱ የዳቦ ማምረቻዎች ለጥያቄ 2.2 አንድ ተብሎ ከተሞላ በኋላ አንድ መጠይቅ መሞላት ሲኖርበት ለዱቄት ፋብሪካው ግን የግድ አንድ ሌላ መጠይቅ መሙላት ያስፈልጋል (በዚህ ጊዜ ጥያቄ 2.2 በሠረዝ መታለፍ ይኖርበታል።)

## 2.3 ፋብሪካው ሥራ የጀመረበት ወርና ዓመት ምህረት መቼ ነው

ፋብሪካው ተቋቁሞ ተግባራዊ ሥራ የጀመረበት ወርና ዓ.ም፣ በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ይመዘገባሉ። ለምሣሌ፣ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪው ሥራ የጀመረው በጥር ወር 1990 ዓ.ም፣ ቢሆን በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ጥር አምተኛ ወር ስለሆነ 051990 ይሞላል ማለት ነው። ፋብሪካው ከተቋቋመ በኋላ የይዞታ ለውጥ ቢያደርግም እንኳን መሞላት ያለበት የተቋቋመበት መሆኑን ማስተዋል ይገባል።**ሆኖም ግን ፋብሪካው የምርት ዓይነት ለውጥ ካደረገ የምርት ለውጥ ያደረገበትን ወቅት መሆን አለበት።**

## 2.4 የማምረቻ ኢንዱስትሪው የሂሣብ መዝገብ ሁኔታ

**የተሟላ የሂሣብ መዝገብ፣** ማለት የፋብሪካውን የወጪና የገቢ መጠን በየወጪና በየገቢው አርዕስት ዘርዝሮ የሚይዝ፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫና የሂሣብ ቋት (Balance Sheet) የሚይዝ መዝገብ ነው። ይህም የሂሣብ መዝገብ ለሂሣብ ቋት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ አዲስ ባላንስ ይዞ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚለወጥ ሲሆን፣ ለትርፍና ኪሣራ መግለጫ ደግሞ በዓመቱ መጀመሪያ በአዲስ ባላንስ የሚጀምር ይሆናል። የዓመቱ መጀመሪያና መጨረሻ ማለት ግን የበጀት ዓመት መጨረሻ ወይም የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር መጀመሪያና መጨረሻ ላይሆን ይችላል።

ከላይ በቀረበው መሠረት ፋብሪካው የሂሣብ መዛግብት የሚይዝ ከሆነ ኮድ «1»፣ የወጪና የገቢ ዝርዝር ብቻ የሚይዝ ከሆነ ኮድ 2፣ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብ የማይዝ ከሆነ ኮድ 3 ከተከበበ በኋላ በተሰጠው ካርድ ኮለም ቁጥሩ መስፈር ይኖርበታል። ፋብሪካው የሂሣብ መዛግብት ካሉት የወጪና የገቢ ዝርዝር (ኦዲት የተደረገም ሆነ ጊዜያዊ) ከመጠይቁ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።

## 2.5 ፋብሪካው የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ከሆነ በየትኛው ዘመን አቆጣጠር ነው?

ለጥያቄ 2.4 የተሰጠው ኮድ 1 ወይም ፋብሪካው የተሟላ የሂሣብ መዝገብ የሚይዝ ከሆነ ፋብሪካው ሂሣቡን የሚይዘው በየትኛው የዘመን አቆጣጠር መሆኑን ለመግለጽ ከ1-4 ከተዘረዘሩት ውስጥ የትክክለኛውን መልስ ኮድ በመክበብ የተከበበዉን ኮድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ውስጥ ማስፈር ያስፈልጋል:: ሆኖም መልሱ በ4ኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ሌላ /ይገለጽ/ ከሆነ አራትን በመክበብና በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ በማስፈር ወሩና ቀኑ ከመቼ እስከ መቼ እንደሆነ በአቅጣጫው በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በጽሁፍ መገለጽ ይኖርበታል:: አማራጭ መልሶቹም፣

በበጀት ዓመት (ከሐምሌ 1 - ሰኔ 30) -------------------------------- 1
በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር (ከመስከረም 1 - ጳጉሜ 5/6) ---------2
በአውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር (ከጃኑዋሪ 1 - ዲሴምበር 31)----3
ሌላ (ይገለጽ) ---------------------------------------- ---------------- 4

## 2.6 የፋብሪካው የባለቤትነት ዓይነት ምንድን ነው?

ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ይህ ፋብሪካ በማን ባለቤትነት ሥር እንደነበር ማለትም በግል/የኅ.ሥ.ማ. ወይም በመንግሥት ይዞታ ሥር መሆኑን ለማመልከት ትክክለኛ ውን ኮድ በመክበብ በተሰጠው ክፍት ቦታ ኮዱን መጻፍ ያስፈልጋል:: የግል/የኅ.ሥ.ማህበር የሚለው በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት፣ በሽርክና/ጆይንት ቬንቸር፣ በባለአክሲዮን ኩባንያነት፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያነት፣ በኅብረት ሥራ ማህበር፣ ፋብሪካዎችን የሚመለከት ነው:: የመንግሥት ማለት ደግሞ በማዕከላዊ መንግሥትና በማዘጋጃ ቤት የተያዙ ፋብሪካዎችን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው:: ነገር ግን የፋብሪካው ይዞታ በመንግሥትና በግል በቅንጅት ከሆነ ኮድ 3 ከተከበበ በኋላ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የእያንዳንዳቸውን ድርሻ በመቶኛ በአጻጻፋቸው ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያው ሠረዝ ላይ የመንግሥትን ድርሻ እንዲሁም በሁለተኛው ሠረዝ ላይ የግሉን ድርሻ በነጠላ ሠረዝ በመለየት መጻፍና ኮዱን በተሰጠው ካርድ ኮለም ማስፈር ያስፈልጋል:: <u>ማሳሰቢያ፦</u> በሽሙር ማህበር /Joint venture/ የተያዘ ፋብሪካ ካጋጠመ በኢትዮጵያ የንግድ ኮድ በሽርክና ስለሚፈረጅ በዚህ ዓምድ ላይ በግል የሚለው ውስጥ ይካተታል:: ለማጠቃለል ያህል በግል ማለት በ2.9 ላይ ከ1 - 5 የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል::

## 2.7 የማምረቻ ኢንዱስትሪው ከመንግሥት ወደ ግል የተዛወረ ነውን?

በጥያቄ 2.6 ኮድ 1 ወይም 3 ለተሞላላቸው በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ፋብሪካው ከተመሠረተ በኋላ ከመንግሥት ወደ ግል በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የተዛወረ ከሆነ ኮድ 1 ካልተዛወረ ደግሞ ኮድ 2 ከተከበበ በኋላ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የተከበበዉን ኮድ መሞላት አለበት::

## 2..8 ለጥያቄ 2.7 መልሱ ኮድ 1 ወይም አዎ ከሆነ ከመንግሥት ወደ ግል የተዛወረበት ወርና ዓ.ም ይገለጽ

ፋብሪካው ከመንግሥት ወደ ግል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዛወረ ከሆነ የተዛወረበት ወርና ዓ.ም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ከተሞላ በኋላ ወርና ዓመቱ በካርድ ኮለሞቹም መሞላት ይኖርበታል::

## 2.9 በተራ ቁጥር 2.6 ኮድ 1 ወይም ኮድ 3 (የግሉ ድርሻ 51 ፐርሰንትና በላይ ከሆነ ብቻ) ለተሞላላቸው የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም ምንድን ነው?

የፋብሪካውን የባለቤትነት ዓይነት በሚመለከት ቀጥሎ የተሰጠውን ትርጉም መሠረት በማድረግ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ትክክለኛውን ኮድ በመክበብ፣ ይኸው ኮድ በተሰጠው የኮድ ቦታ መጻፊያ ላይ ይሞላል::

ማስታወሻ፣ ለጥያቄ 2.6 ኮድ 3 ለተሞላላቸው ፋብሪካዎች የመንግሥት ድርሻ እኩል ወይም የሚበልጥ (50% እና በላይ) ከሆነ ይህ ጥያቄ በሠረዝ መታለፍ አለበት::

1. በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት የሚመራ:- ፋብሪካው በአንድ ግለሰብ ባለቤትነት የተያዘ ሲሆን ነው::

2. ሽርክና:- ማለት ሕጋዊ ሰውነት ያለው ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ሆኖ ከአንድ በበለጡ ግለሰቦች ባለቤትነት የሚካሄድ ፋብሪካ ነው:: ሽሙር ማኅበር /Joint venture/ በአብዛኛው በኢትዮጵያውያንና በውጭ ዜጎች የጋራ ባለቤትነት የተመሠረተ ፋብሪካን ያጠቃልላል:: ስለዚህ የዚህ ዓይነት ድርጅት/ፋብሪካ ካጋጠመን በሽርክና ውስጥ ይሞላል::



1990 ዓ.ም

3. <u>ባለ አክሲዮን ኩባንያ</u> :- ኃላፊነቱ የተወሰነ ሆኖ በአምስት ወይም ከአምስት በላይ በሆኑ ግለሰቦች ስምምነት የተቋቋመ ነው:: አክሲዮኖቹ ከአንድ ግለሰብ ወደ ሌላ የባለቤትነት ስም ለማዛወር ይቻላል::

4. <u>ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ</u>: ኃላፊነቱ የተወሰነ ሆኖ በሁለት ወይም ብዛታቸው ከሃምሳ በማይበልጥ ግለሰቦች የሚቋቋም ነው:: አክስዮኖቹን ከአንድ ግለሰብ ወደ ሌላ የባለቤትነት ስም ለማዛወር የሚቻለው ከአባላቱ 3/4ኛው ሲፈቅድ ነው::

5. <u>የህብረት ሥራ ማህበር</u>:- ከአንድ የበለጡ ግለሰቦች ወይም ቤተሰቦች ንብረታቸውንና ዕውቀታቸውን በማስተባበር ራሳቸው በሥራው ተካፋይ በመሆን በጋራ ባለቤትነትና አመራር የሚያካሂዱት ድርጅት ነው:: <u>ማሳሰቢያ</u>: የህብረት ሥራ ማህበር ከሽርክና የሚለየው ተመሳሳይ ሞያ ያላቸው ሰዎች የሚያቋቁሙት በመሆኑ ነው::

6. <u>ሌላ</u>:- ከ1-5 ከተዘረዘሩት አማራጮች ውጭ ከሆነ ሌላ በሚለው አቅጣጫ 6 ቁጥር ይከበብና የባለቤትነቱን ዓይነት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በመጻፍ የተከበበው ኮድ በተሰጠው ካርድ ኮለም ውስጥ ይሰፍራል:: (ለምሳሌ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም አብዛኛው ድርሻቸው በተለያዩ ድርጅቶች የተያዘ ከሆነ ኮድ 6 ይሞላል ማለት ነው)

## 2.10 <u>በ2.9 የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም ለተሞላላቸው የፋብሪካው ባለቤቶች ብዛት በፆታ ይገለጽ፣</u>

በ2.9 የፋብሪካው ሕጋዊ አቋም ለተሞላላቸው የግል/የኅብረት ሥራ ማህበር ለሆኑት በፋብሪካው ሥራ የሚሳተፉም ሆነ የማይሳተፉ ባለቤቶችን ብዛት በፆታ በመለየትና በመደመር መመዝገብ ያስፈልጋል:: ስለሆነም በመንግሥት ወይም በማዘጋጃ ቤት ወይም በመንግሥትና በግል ይዞታ ሥር ያሉትን ፋብሪካዎች ይህ ጥያቄ አይመለከታቸውም:: ሆኖም በመንግስትና በግል ይዞታ ላሉ የግሉ ይዞታ 51 ፐርሰንትና በላይ ከሆነ ይህ ጥያቄ መጠየቅ ይኖርበታል:: በተጨማሪም በተራ ቁጥር 2.9 ላይ ኮድ 6 የተሞላላቸውና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ለተያዙ ፋብሪካዎች ይህ ጥያቄ አይመለከታቸውም::

## 2.11 ማምረቻ/ ድርጅቱ የማምረት ሥራዉን ሲጀምር የመነሻ ካፒታል መጠን በባለቤትነት ዓይነትና በፆታ ይገለጽ::

የመነሻ ካፒታል ሲባል የማምረቻ ድርጅቱ ሲቋቋም የድርጅቱ ባለቤቶች ሥራውን ለመጀመር ያወጡት/የከፈሉት የገንዘብ መጠንን ይመለከታል:: ይህ የገንዘብ መጠን የድርጅቱን ሥራ ለመጀመር ቋሚ ንብረቶችን ለመግዛት/ለመሥራት ያዋጡትንና ለሥራ ማስኬጂያ የከፈሉትን የገንዘብ መጠን በሙሉ የሚያካትት መሆን ይገባዋል:: በዚህ መሠረት ኢትዮጵያውያንን በፆታ በመለየት ኢትዮጵያዊ ካልሆኑ በፆታ ሳይለይ የተዋጣውን የገንዘብ መጠን በብር በየአንፃራቸው በተሰጠው ክፍት ቦታ ከተሞላ በኋላ፣ ከጎኑ ባሉት ካርድ ኮለሞች ውስጥ የገንዘቡ መጠን ተደግሞ ይሞላል:: አማራጭ መልሶቹም::

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ኢትዮጵያዊ ወንድ | ብር________ |
| 2. | » ሴት | ብር________ |
| 3. | » ያልሆነ | ብር________ |
| 4. | የመንግሥት | ብር________ |
| 5. | ሌላ /ይገለጽ/ | ብር________ |
| 6. | ድ ም ር | ብር________ |

ማሳሰቢያ:- ድርጅቱ መነሻ ካፒታሉን ከብድርም ሆነ ከራሱ ወይም ከማንኛውም ምንጭ ሊያገኘው ይችላል::

## 2.12 ፋብሪካው የደረሰበት ካፒታል (End Year Capital) መጠን በባለቤትነት ዓይነትና በፆታ ይገለጽ፣

የደረሰበት ካፒታል ሲባል የአክሲዮን ባለቤት በሆኑት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የተከፈለውን የገንዘብ መጠን ይመለከታል:: ይህ የገንዘብ መጠን የፋብሪካውን ሥራ ለመጀመር ማለትም ቋሚ ንብረቶችን ለመግዛት/ለመሥራት ያዋጡትንና ለሥራ ማስኬጂያ የከፈሉትንና ፋብሪካውን ለማስፋፋት እስከ ጥናቱ ዓመት መጨረሻ ድረስ የከፈሉትን የገንዘብ መጠን እንዲሁም በየዓመቱ ከሚገኘው ትርፍ ለፋብሪካው ማስፋፊያ የተደረገውን በሙሉ የሚያካትት መሆን ይገባዋል:: በዚህ መሠረት ኢትዮጵያዊያንን በፆታ በመለየት፣ ኢትዮጵያዊ ካልሆኑ በፆታ ሳይለይ የተዋጣውን የገንዘብ መጠን በብር በየአንፃራቸው በተሰጠው ክፍት ቦታ ከተሞላ በኋላ፣ ከጎኑ ባሉት ካርድ ኮለሞች ውስጥ የገንዘቡ መጠን ተደግሞ ይሞላል:: አማራጭ መልሶቹም፣

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ኢትዮጵያዊ ወንድ | ብር________ |
| 2. | « ሴት | ብር________ |
| 3. | « ያልሆነ | ብር________ |
| 4. | የመንግሥት | ብር________ |
| 5. | ሌላ /ይገለጽ/ | ብር________ |
| 6. | ድ ም ር | ብር________ |

ማሳሰቢያ፡- ፋብሪካው የደረሰበት ካፒታል ከብድርም ሆነ ከራሱ ወይም ከማንኛውም ምንጭ ሊያገኘው ይችላል።

## 2.13 ፋብሪካው በ2004 ዓ.ም ለምን ያህል ወራት ሠራ (በሙሉ ወር ይገለጽ)

በጥናት ዓመቱ ውስጥ ፋብሪካው ለስንት ወራቶች እንደሠራ በመጠየቅ በሙሉ ወር በተሰጡት ካርድ ኮለሞች መሙላት ያስፈልጋል። መልሱ በሚሞላበት ወቅት በክፍልፋይ ደንብ መሠረት በማጠጋጋት መሞላት ይኖርበታል። የፋብሪካው የሥራ ወራቶች በጥሬ ዕቃ እጥረትና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት ያልሠራበትን ወራት እንዲሁም ረዘም ላለ ጊዜ ለወቅታዊ ጥገናና እንክብካቤ ሥራውን ቢያቋርጥ እንደሰራ አይቆጠርም። ወቅታዊ ጥገናና እንክብካቤ ማለት የአንድን ቋሚ ንብረት የአገልግሎት ዘመን ለማራዘም የሚደረግ ጥገና ሳይሆን የንብረቱን ቅርጽ ወይም መልክ ለማሳመር ወይም ንብረቱ በነበረበት ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚደረግ ጥገና ነው።

## 2.14 ፋብሪካው ሙሉውን ዓመት ካልሠራ ያልሠራበት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች በቅደም ተከተላቸው መሠረት ይገለጹ።

ፋብሪካው **ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት 12 ወራት ካልሠራ** ካልሠራባቸው ምክንያቶች መካከል ዋና ዋና የሆኑት ሦስቱ ምን ምን እንደነበሩ ተጠይቆ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር የሚዛመዱት ኮዶች ይከበቡና የመጀመሪያው ዋና ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 23፣ የሁለተኛው ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 24 እና የሦስተኛው ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 25 ውስጥ ይጻፋል። በተቻለ መጠን ዋናዎቹ ምክንያቶች ከፋብሪካው ባለቤት ወይም ወኪል እንዲገለጽ ማድረግ እንጂ የተዘጋጁትን አማራጭ መልሶች ለባለቤቱ አስቀድሞ መዘርዘሩ የሚገኘውን መልስ የተዛባ ሊያደርገው ይችላል።

አማራጭ መልሶቹም፣

አዲስ በመሆኑ-----------------------------------------=01

የጥሬ ዕቃዎች እጥረት--------------------------------=02

የመለዋወጫዎች እጥረት-----------------------------=03

የውጭ ምንዛሬ ችግር ---------------------------------=04

የገበያ ችግር-------------------------------------------=05

በቂ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል ማጣት-----------------=06

የመብራትና የውኃ አገልግሎት መቋረጥ--------------=07

የማምረቻ መሣሪያዎች በየጊዜው መበላሸት----------=08

የመንግሥት ህጎችና ደንቦች ጫና-----------------------=09

ሌላ /ይገለጽ/ ______________________________ =10

## 2.15 ፋብሪካው የሚገለገልበት የማምረቻ ህንፃ (ቤት) ይዞታ፣

ፋብሪካው የሚገለገልበት ህንፃ (ቤት) ይዞታ የግል ከሆነ ማለትም በፋብሪካው ባለቤትነት የተያዘ ከሆነ ኮድ 1፣ በኪራይ የተያዘ ከሆነ ኮድ 2 ከተከበበ በኋላ የተከበበዉ ኮድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: ሆኖም መልሱ ከዚህ ውጭ ከሆነ ኮድ 3 ከተከበበ በኋላ የይዞታውን ዓይነት በቀሰጠው ክፍት ቦታ ላይ መግለጽ ያስፈልጋል::

## ክፍል 3 - በ2004 ዓ.ም. በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ (በብር)

በዚህ ክፍል የሚሞላው በጥናቱ ዓመት ውስጥ በፋብሪካው ሥራ ላይ ተካፋይ የሆኑ ሰዎች (ቋሚ፣ኮንትራት፣ጊዜያዊና ተለማማጅ) ብዛትና ፋብሪካው ለሠራተኞች የከፈለውን ደመወዝና ምንዳ በሚመለከት ይሆናል። በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሰዎች ሲባል ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ በፋብሪካው ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለንብረቶች፣ ሽርኮችና በስራው ተካፋይ የሆኑ ሳይከፈላቸው የሚሠሩ የቤተሰብ አባላት፣ ተለማማጆች፣ በሥራው ተካፋይ የነበሩ የህብረት ሥራ ማህበር አባላትና በስራው ተካፋይ የነበሩ ቅጥር ሠራተኞችን በሙሉ እና የቦርድ አባል ሆነው ቋሚ ደመወዝ ያላቸውን ያጠቃልላል። ሆኖም ግን የቦርድ አባል ሆኖ በተሰበሰበ ቁጥር ብቻ ክፍያ የሚያገኝ ሠራተኛ መካተት የለበትም። በጥናት ዓመቱ እየተከፈላቸው በሕክምና ወይም የዓመት ፈቃድ ላይ የነበሩ ሠራተኞችን ማካተት ይኖርበታል። የሰው ኃይልን በሚመለከት በጥናት ዓመቱ ፋብሪካው ከሠራባቸው ወራቶች ውስጥ በመጠይቁ ላይ በተጠቀሱት ወራት ውስጥ ብቻ (መስከረም፣ ታህሣሥ፣ መጋቢትና ሰኔ) የነበሩትን ሠራተኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ በማለት በአጠቃላይ የሙያ መደብ ዓይነት ለይቶ ማሳየት ያስፈልጋል። ደመወዝና ምንዳን በሚመለከት ደግሞ የዓመቱን ጠቅላላ በመደመር ለጊዜያዊ ሠራተኞች በ3.1 በተራ ቁጥር 6 አቅጣጫ ዓምድ 16 ውስጥ መሞላት ሲኖርበት ለቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ደግሞ በ3.2 በሙያ መደብ፣ በጾታና በዜግነት ተለይቶ መቅረብ ይኖርበታል።

### 3.1 በ2004 ዓ.ም. በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ብዛት፣

ዓምድ 2 - አጠቃላይ የሙያ መደብ

1. ሳይከፈላቸው በሥራው ተካፋይ የሆኑ ባለንብረቶች፣ ሽርኮች፣ የህብረት ሥራ ማህበር አባላትና ሳይከፈላቸው የሚሠሩ የቤተሰብ አባል የሆኑ ሠራተኞች፣ ሳይከፈላቸው የሚሠሩ ባለንብረቶችና ቤተሰቦቻቸው፣ ሥራው በሽርክና የሚሠራ ከሆነ በሥራው ተካፋይ የሆኑትን፣ እንዲሁም ሥራው በህብረት ሥራ ማህበር የሚካሄድ ከሆነ ሳይከፈላቸው በሥራው ተካፋይ የሆኑ የህብረት ሥራ ማህበር አባላት ሁሉ ብዛታቸዉ ከዓምድ 3-14 ባለዉ ቦታ መሞላት ይኖርበታል
2. ተለማማጅ የማይከፈላቸው፣ በፋብሪካው ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ወይም የሥራ ዓይነት በመለማመድ ላይ የሚገኙና ደመወዝ ወይም ድጎማ የማይከፈላቸው በተጠቀሱት ወራት ውስጥ በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች በየታ ተለይተው ብዛታቸዉ ከዓምድ 3-14 እንደአስፈላጊነቱ ይሞላል።

3. አስተዳዳሪዎች፣ የቴክኒክ ሠራተኞች፣ ፀሐፊዎችና ሌሎች የቢሮ ሠራተኞች፣ ከምርት ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው በቋሚነትና በኮንትራት ተቀጥረው ደመወዝ የሚከፈላቸው ሥራ አስኪያጆች፣ ዲያሬክተሮች፣ ቴክኒሺያኖች፣ ተቆጣጣሪዎች፣ የምርምር ሠራተኞች፣ የንድፍ ሥራ አዋቂዎች፣ ቅርጽ ሠሪዎች፣ ኢንጂነሮች፣ ገንዘብ ያዦች፣ የጽሕፈት ሠራተኞች፣ ሾፌሮች፣ አስተናጋጆች፣ አሻሻጮች፣ ዕቃ አዳዮችና ተቀባዮች፣ ዘበኞች፣ የአስተዳደር ሠራተኞችና ሌሎች የቢሮ ሠራተኞች ብዛት ከአምድ 3-14 ባላዉ ቦታ ይሞላል::

4. በምርት ተግባር በቀጥታ ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች፣ አርዕስቱ እንደሚያመለክተው በዚህ ንዑስ የሙያ መደብ የሚመደቡት ከምርት ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን ቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ማለትም በማምረት፣ በማስናዳት፣ በመገጣጠም፣ መሣሪያ በማቀበል፣ በመቆጣጠር፣ ዕቃ በመጠቅለል፣ በዕቃ ግምጃ ቤትነት፣ በዕቃ ላኪነት፣ በእድሳትና ጥገና፣ በጽዳት ሥራ፣ በስቶክ መዝጋቢነት እና ሌሎችም ከምርት ሥራ ጋር በተያያዙ የአገልግሎት ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ብዛት ከአምድ 3-14 ባላዉ ቦታ ይሞላል::

4.1 ቋሚ ሠራተኛ:- ቋሚ ሠራተኛ ማለት በድርጅቱ ሥራ ተካፋይ የሆነና ላልተወሰነ ጊዜ በደመወዝ ተቀጥሮ የሚሠራ ሠራተኛ ማለት ነው:: ነገር ግን በሠራተኛውና በአሰሪው መካከል በተደረገ የቃል ወይም የጽሑፍ ስምምነት መሠረት የቅጥር ሁኔታው ሊቋረጥ የሚችለውን ጊዜያዊ ወይም ኮንትራት ሠራተኛን አይጨምርም::

4.2 ኮንትራት ሠራተኛ :-ለዚህ ጥናት ኮንትራት ሠራተኛ ማለት በድርጅቱ ባለቤትና በሠራተኛው መካከል በሚደረግ የጽሑፍ ስምምነት መሰረት የተቀጠረዉን ሠራተኛ ነዉ፡፡የተደረገው ስምምነት ሊታደስ ወይም ሊቋረጥ ይችላል:: ክፍያዉም በቀን፣በሳምንት..ወዘተ ሊሆን ይችላል::

5. ተለማማጅ የሚከፈላቸው፣ በፋብሪካው ውስጥ በየትኛውም ደረጃ ወይም የሥራ ዓይነት በመለማመድ ላይ የሚገኙና ደመወዝ ወይም ድጎማ እየተከፈላቸው በተጠቀሱት ወራት ውስጥ በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች በያታ ተለይተው ከዓምድ 3-14 እንደአስፈላጊነቱ ይሞላል::

6. ጊዜያዊ ሠራተኞች፣ በሠራተኛውና በአሠሪው መካከል በተደረገው የቃል ስምምነት መሠረት በጥናት ዓመቱ በሙሉ ወይም ለተወሰነ ጊዜ የሠሩ ሠራተኞች ስዎች በወራት ተሰልቶ በኣምድ 15 ይሞላል ምንዳዉም በዓምድ 16 ይሞላል:: በተጨማሪም እነዚህ ሠራተኞች በደመወዝ መክፈያ ሊስት ላይ በአብዛኛው ለብዙ ወራት የማይታዩ ናቸው::

7. ድምር፣ በየዓምዶቹ ውስጥ የተጻፉትን ቁጥሮች ቁልቁል በመደመር በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይመዘገባሉ::

14+3.1+2+0.4+0.3

<u>ከዓምድ 3 - 14 - በ2004 ዓ.ም. በተጠቀሱት ወራቶች የደመወዝ መክፈያ ሊስት ላይ ወይም የመጨረሻው የሥራ ቀን ላይ የነበሩ ሠራተኞች ብዛት</u>፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ በተጠቀሱት ወራት (መስከረም፣ ታህሣሥ፣ መጋቢትና ሰኔ) በነበረው የመጨረሻ የሥራ ቀን ወይም ደመወዝ በተከፈለበት ቀን ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ሠራተኞችን በፆታ በመለየት እንዲሁም ኢትዮጵያዊያን ያልሆኑ ሠራተኞች ስንት እንደነበሩ ብዛታቸው በፆታ ሳይለይ በየዓምዱ ይመዘገባል::

<u>ዓምድ 15 - ሰዎች በወራት (Person/Months)</u>፣ በተራ ቁጥር 6 አቅጣጫ በዓምድ 2 ሥር በተጠቀሰው የጊዜያዊ ሠራተኞች አንፃር በዓምድ 15 ጊዜያዊ ሠራተኞች የሠሩትን ወራት በብዛታቸው በማባዛት የተገኘው ቁጥር ይመዘገባል:: <u>ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ለተወሰኑ ጊዜያት ወይም ዓመቱን በሙሉ የነበሩትን ጊዜያዊ ሠራተኞች አንድ በአንድ በመቁጠር ብዛታቸውን በሠሩበት ወራት በማባዛት መመዝገብ እንጂ ማዕከላዊ ቁጥር (Average) መወሰድ የለበትም</u>:: ስለሆነም ሰዎች በወራት በምናሰላበት ወቅት በፋብሪካው የነበሩ ጊዜያዊ <u>የሠራተኞች</u> ብዛት በጥናት ዓመቱ በሁሉም ወራት የማይለዋወጥ ከሆነ የአንዱን ወር የጊዜያዊ <u>ሠራተኞች</u> ብዛት ጠቅላላ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ በሠሩት ወራት በማባዛት ሰዎች በወራት ይገኛል:: ነገር ግን የጊዜያዊ ሠራተኞች ብዛት በየወሩ የሚለዋወጥ ከሆነ ተመሳሳይ የወራት ብዛት የሠሩትን ለየብቻ በማስላትና የተገኘ ውን ቁጥር አንድ ላይ በመደመር መመዝገብ ያስፈልጋል::

8x

*<u>ምሣሌ</u>:- አንድ የጫማ ፋብሪካ*
*ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ውስጥ 10 ጊዜያዊ ሠራተኞች ቀጥሮ አሰርቶ*
*ከሆነና ከእነዚህም ውስጥ:-*
*2 ሠራተኞች ለ4 ወራት ከ12 ቀናት*
*1 ሠራተኛ ለ2 ወራት ከ15 ቀናት*
*4 ሠራተኞች ለ7 ወራት ከ5 ቀናትና*
*3 ሠራተኞች ለ25 ቀናት ቢሠሩ ሰዎች በወራት ለማግኘት እንደሚከተለው ይሰላል::*

4 ) 34

| የጊዜ ርዝማኔ እና የሠሩ ሠራተኞች ብዛት | እያንዳንዳቸው የሠሩት የጊዜ ርዝማኔ | ሰው ወራት/Man months/ |
|---|---|---|
| 2 | 4 ወር ከ12 ቀን | 2(4+12/30 ) =8.80 |
| 1 | 2 ወር ከ15 ቀን | 1(2+15/30) = 2.50 |
| 4 | 7 ወር ከ5 ቀን | 4(7+5/30)= 28.67 |
| 3 | 0 ወር ከ25 ቀን | 3(25/30) = 2.50 |
| ድምር | | 42.47 |

ስለዚህ ጠቅላላ የሰው ወራት 42 ይሆናል ማለት ነው::

15 ቀን: 28
16 ቀን = 1
30 ቀን = 2
11 ቀን = 1
7.5 ቀን = 1

28 (15/30) =
2 (16/30) =
2 (30/30) =
1 (11/30) =
1 (8/30)

ዓምድ 16 - ምንዳ (Wages)፣ በተራ ቁጥር 6 በዓምድ 2 ሥር በተጠቀሰው በጊዜያዊ ሠራተኞች አቅጣጫ በዓምድ 16 ሥር ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ለጊዜያዊ ሠራተኞች የተከፈለውን ጠቅላላ ምንዳ (የደመወዝ መጠን) ይመዘገባል:: የምንዳ መጠን **ሲመዘገብ መረሳት የሌለበት በጥናት ዓመቱ በተለያዩ ጊዜያት የተሠናበቱም ሆነ ያልተሠናበቱ በጠቅላላው በፋብሪካው በጊዜያዊነት ይሠሩ ለነበሩ ሠራተኞች የተከፈለውን** ዓመታዊ የምንዳ (ደመወዝ) መጠን መሆን ይኖርበታል::

ማስታወሻ : ይህ ክፍል የሠራተኛ ብዛት፣ ደመወዝና ምንዳ ከምንዘረዝርበት ባሻጋር የማምረቻ ኢንዱስትሪው በትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ ውስጥ መካተቱን የምናረጋግጥበት ነው:: በመሆኑም በተጠቀሱት ወራቶች (መስከረም፣ ታህሣሥ፣ መጋቢት እና ሰኔ) የሚገኙት የሠራተኞች ብዛት ተደምሮ ለአራት በማካፈል እና በዓምድ 15 (ሰዎች በወራት) የተሞላውን ለ12 ወራት በማካፈል ከደመርን በኋላ ድምሩ 10 እና ከዚያ በላይ ከሆነ የማምረቻ ድርጅቱ በጥናቱ የሚካተት ይሆናል:: ይህ የሚሆነው ድርጅቱ ለ12 ወራት የሠራ ከሆነ ነው 12 ወር በሙሉ ካልሠራ ግን ሰዎች በወራትን የምናካፍለው የማምረቻ ድርጅቱ ለሠራበት ወራት ነው::

ምሳሌ /አስራ ሁለት ወራት ለሠራ ድርጅት/

| | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| መስከረም | 4 | 3 | 7 |
| ታህሣሥ | 3 | 2 | 5 |
| መጋቢት | 7 | 3 | 10 |
| ሰኔ | 3 | 4 | 7 |
| **ድምር** | | | 29 |

ሰዎች በወራት = 48 በዓምድ 15 ቢሞላ

29/4 + 48/12 = 11 የተገኘው ውጤት 7+4=11 በመሆኑ የማምረቻ ድርጅቱ በጥናቱ የሚካተት ይሆናል::

## 3.2 በ2004 ዓ.ም. የተከፈለ ደመወዝ፣ ምንዳ እንዲሁም ሌሎች የሠራተኛ ጥቅሞች (በብር)

ከዓምድ 3-5 - ቅንስናሽ ሳይደረግ የተከፈለ የዓመቱ ጠቅላላ ደመወዝ፣ በአጠቃላይ የሙያ መደቡ (በዓምድ 2 ሥር ለተዘረዘሩት) ለተሠማሩት ቅጥር ሠራተኞች ኢትዮጵያዊያንና (ወንድና ሴት በመለየት) ኢትዮጵያዊያን ላልሆኑ ሠራተኞች (በፆታ ሳይለይ) ቅንስናሽ ሳይደረግ (የገቢ ግብር ሳይቀነስ) ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ የተከፈለው ደመወዝ

በየዓምዶቹ ይመዘገባል:: በበዓል፣ በዕረፍት ጊዜ የተከፈለውንና ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ የሚቀነሱ ልዩ ልዩ እንደ ገቢ ግብር የመሳሰሉ ታክሶችን ማጠቃለል እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል::

ዓምድ 6 - ድምር፣ በዚህ ዓምድ ሥር የዓምድ 3፣ 4 እና 5 ድምር ይመዘገባል::

ዓምድ 7 - ኮሚሽን፣ ቦነስ፣ የበረሃ አበልና ልዩ ልዩ አበሎች (የቀን አበልንና የነዳጅ አበልን አይጨምርም)፣ በተራ ቁጥር 4 በዓምድ 2 ድምር የሚለውን አቅጣጫን በመከተል በዓምድ 7 ሥር ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው ለሠራተኞች የከፈለውን ኮሚሽን፣ ቦነስ፣ የበረሃ አበልና ልዩ ልዩ አበሎች አንድ ላይ በመደመር ይመዘገባል::

ዓምድ 8 - ለምግብ፣ ለቤት ኪራይ፣ ለትምህርት፣ ለሕክምናና ለመሳሰሉት በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ ፋብሪካው ለሠራተኞች ያደረገው ወጭ፣ በተራ ቁጥር 4 በዓምድ 2 ድምር የሚለውን አቅጣጫ በመከተል በዓምድ 8 ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ለሠራተኞች ያወጣው ወጭ ይመዘገባል:: ፋብሪካው ለሠራተኞች በቅናሽ የሸጠው ዕቃ ወይም ግልጋሎት ካለ የሚመዘገበው ቅናሽ የተደረገው የገንዘብ መጠን ብቻ ነው:: ነገር ግን በሥራው ሂደት ላይ የተሻለ ውጤት ለማግኘት ሲባል ለሠራተኛው የሚሰጡ እንደ ዩኒፎርም እዚህ ውስጥ መካተት የለባቸውም::

ዓምድ 9 - ፋብሪካው ለሠራተኞች ለጡረታና ለሕይወት ኢንሹራንስ የከፈለው፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ በቀጣሪው የሚሸፈኑ የሠራተኛ ጡረታ፣ የኢንሹራንስ መዋጮ እና የመሳሰሉት በዓምድ 2 ተራ ቁጥር 4 ድምር በሚለው አቅጣጫ ዓምድ 9 ሥር ይመዘገባሉ::

ዓምድ 10 - የፈረቃ ብዛት፣ አንድ ፈረቃ ማለት 8 ሰዓት መደዳውን መሥራት ነው:: ስለዚህ በዚህ ዓይነት በምርት ተግባር በቀጥታ ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች በቀን በስንት ፈረቃ ተደልድለው እንደሚሠሩ በተራ ቁጥር 3 አቅጣጫ በዓምድ 10 ሥር መመዝገብ ያስፈልጋል::

## 3.3 በ2004 ዓ.ም. የቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ብዛት በሚያገኙት መደበኛ ደመወዝ መጠን አመዳደብ፣

12600
1400
24000

በሰኔ ወር የመጨረሻ ሣምንት ወይም ቀን ላይ የነበሩ ቋሚና ኮንትራት ሠራተኞችን የደመወዝ መክፈያ ሊስት በመውሰድ በሚያገኙት መደበኛ የደመወዝ መጠን መሠረት (የትርፍ ሰዓት ክፍያን ሳይጨምር) ጠቅላላ የፋብሪካውን ሠራተኛ በፆታ በመለየት ከዓምድ 3-10 ከፋፍሎ መሙላት ያስፈልጋል:: ዓምድ 11 ቁልቁል ሲደመር የሚገኘው ውጤት በሰኔ

ወር ላይ በመጠይቁ ክፍል 3.1 ዓምድ 12፣ 13 እና 14 በተራ ቁ.. 3 እና 4 አቅጣጫ የተሞላውን በመደመር ከሚገኘው ውጤት ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።

## ክፍል 4 - በ2004 ዓ.ም በፋብሪካው የተመረቱና የተሸጡ ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ ሊያመርት የሚችለው ጠቅላላ የምርት ዋጋ በብር

### 4.1 በ2004 ዓ.ም በፋብሪካው የተመረቱና የተሸጡ ዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች እንዲሁም ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ ሊያመርት የሚችለው ጠቅላላ የምርት ዋጋ /ዋጋ በብር/

ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ የተመረቱት (ቢሸጡም ባይሸጡም) እና ጥናቱ ከሚመለከተው ዓመት በፊት ተመርተው በጥናቱ ዓመት የተሸጡትን ዋና ምርቶች ይመለከታል።

ዓምድ 2 - ፋብሪካው የሚያመርታቸው ዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች፣ በዚህ ዓምድ የዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች ስም ዝርዝር ይጻፋል። ዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች ከተመዘገቡ በኋላ የተቀሩትን በአንድነት ሌሎች በሚለው አቅጣጫ ይመዘገባሉ። ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ከእያንዳንዱ ምርት ከሽያጭ የተገኘው ገቢ እንደቅደም ተከተላቸው ዋና ዋና የሆኑትን ምርቶችና ሌሎች ምርቶች ለመመዝገብ መጠቀም ያስፈልጋል።

ማስታወሻ:- ዓምድ 2 ላይ ሌሎች ተብለው በአንድነት የገቡት ዝርዝራቸው በሌላ ወረቀት ተጽፎ መያያዝና ከዓምድ 3-12 እንደየአስፈላጊነቱ መሞላት ይገባዋል።

ዓምድ 3 - መስፈሪያ፣ የፋብሪካው ምርት መጠን በሜትሪክ ሲስተም መስፈሪያ መሰጠት አለበት። ይኸውም ለምሣሌ፣

ሀ. ለምግብ ኢንዱስትሪ፣

1. የሥጋ ውጤት በኪሎ ግራም መሰጠት አለበት እንጂ በቆርቆሮ መሆን የለበትም።
2. የወተት ውጤት በሄክቶ ሊትር።
3. የጨው፣ የዘይት፣ የስኳር፣ የስንዴ ዱቄት፣ የማካሮኒና ከስኳር የተሠሩ ጣፋጭ ምግቦች፣ የብስኩት ውጤቶች በቶን መሰጠት አለባቸው።

ለ. ስመጠጥ ኢንዱስትሪ፣

የምርቱ መጠን መስጠት ያለበት በሄክቶ ሊትር እንጂ በጠርሙስ ቁጥር መሆን የለበትም።

ሐ. ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ፣

1. ድርና ማግ በቶን
2. ጨርቃ ጨርቅ በሜትር ካሬ
3. ብርድ ልብስ በቁጥርና በካሬ ሜትር ገጽ 55 ባለው መሠረት ይሞላል
4. ምንጣፍ በሜትር ካሬ
5. ጆንያ በኪሎ ግራም መስጠት አለባቸው።

**ማስታወሻ፣ ዝርዝር የመስፈሪያ አጠቃቀም ከዚህ አሞላል መመሪያ መጨረሻ ላይ የተያያዘ ስለሆነ በዚሁ መሠረት መሞላት ይኖርበታል።**

ዓምድ 4 - የዋና ምርቶች ኮድ፣ ለቢሮ ስራ ክፍት ይተዋል።

ዓምድ 5 - የመስፈሪያ ኮድ፣ ለቢሮ ስራ ክፍት ይተዋል።

ዓምድ 6 - የአንድ ዕቃ መካከለኛ የሽያጭ ዋጋ (ዕቃው ፋብሪካውን ለቆ ሲወጣ)፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ዕቃው ፋብሪካውን ለቆ ሲወጣ በሚያስገኘው የሽያጭ ዋጋ መሠረት በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች መካከለኛ ዋጋ (Average Price) በማስላት ይመዘገባል። **ዕቃው ፋብሪካውን ለቆ ሲወጣ ያለው ዋጋ የሽያጭ ታክሶችን ማካተት አለበት።**

ማስታወሻ፣ ይህ ዓምድ በሁለት የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያው ለብር መፃፊያ ብቻ ሲሆን ሁለተኛው ለሣንቲም መፃፊያ የሚያገለግል ነው።

ዓምድ 7 - የተመረተው ብዛት፣ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች በዓምድ 3 የተጠቀሰውን መስፈሪያ በመጠቀም ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ የተመረተው መጠን ይመዘገባል።

ዓምድ 8 - ጠቅላላ የምርት ዋጋ (ምርቱ ፋብሪካውን ለቆ ሲወጣ)፣ በዓምድ 6 የተሰጡትን የእያንዳንዱ ዕቃ መካከለኛ የሽያጭ ዋጋ በየአንጻራቸው በዓምድ 7 ከተዘረዘሩት መጠን ጋር በማባዛት የተገኘው ውጤት ለእያንዳንዱ ዋና ዋና ምርትና ሌሎች ምርቶች በዓምድ 8 ውስጥ ይመዘገባል።

ማስታወሻ፣ በዓምድ 7 እና 8 የሚሞላው መጠንና ዋጋ ከክምችት (ከስቶክ) በማውጣት የሚሸጠውን ያለፉት ዓመታት ምርት መጨመር የለበትም።

ዓምድ 9 እና 10 - ጠቅላላ የምርት ሽያጭ፣ ጥናቱ ከሚመለከተው ዓመት በፊትም ሆነ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ተመርተው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ በዱቤ ወይም እጅ በእጅ የተሸጡትን ዋና ዋና ምርቶችና ሌሎች ምርቶች በዓምድ 3 በተጠቀሰው መስፈሪያ መሠረት ብዛታቸው በዓምድ 9 ውስጥ ይመዘገባል:: ይኸውም ዕቃው ፋብሪካውን ለቆ ሲወጣ የሚጨመሩትን ልዩ ልዩ የተሰበሰቡ የተጨማሪ እሴት ታክስና የሽያጭ ታክሶችን ያጠቃልላል::

ዓምድ 11 እና 12 - ከጠቅላላ ሽያጭ ውስጥ ወደ ውጭ አገር የተላከ፣ በዓምድ 3 በተዘረዘረው መስፈሪያ መሠረት ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ከጠቅላላ ሽያጭ (በአምድ 9 እና 10 ከተሞላው ውስጥ) ወደ ውጭ አገር የተላከው መጠን ለእያንዳንዱ ዋና ዋና ምርት በዓምድ 11 ውስጥ ይመዘገባል:: ከጠቅላላ ሽያጭ ላይ ወደ ውጭ የተላከው ምርት የሽያጭ ዋጋ ደግሞ ለእያንዳንዱ ዋና ዋና ምርት በዓምድ 12 ውስጥ ይሞላል::

ዓምድ 13 - ድርጅቱ በ 2004 ዓ. ም. በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ ጠቅላላ የምርት ዋጋ (በገበያ ዋጋ ቢሸጥ)፣ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት የምርት ዓይነቶች በየአንጻራቸው በዓምድ 3 በተዘረዘረው መስፈሪያ መሠረት ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ ቢሠራ (**ድርጅቱ ሲገነባ የ ማምረት አቅሙ (designed) የተደረገዉ**) ሊያመርታቸው የሚችለው ምርቶች በገበያ ዋጋ ቢሸጡ ምን ያህል እንደሆነ የሚሞላ ሲሆን ጠቅላላ ድምሩም ቁልቁል በመደመር በተራ ቁጥር 12 ድምር በሚለው አቅጣጫ መሙላት ያስፈልጋል::

## 4.2 የማምረቻ ድርጅቱ በ2004 ዓ.ም. ያመረተው የመርት መጠን ከማምረት አቅሙ ምን ያህል እንደሆነ በመቶኛ ይገለጽ

የማምረቻ ኢንዱስትሪው በ2004 የምርት ዘመን ያመረተው የምርት መጠን ከማምረት አቅሙ (designed) ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል እንደሆነ በመቶኛ ተጠይቆ በተሰጠው ባዶ ቦታ መሞላት ይኖርበታል:: በዚህ ቦታ የፋብሪካውን የማምረት አቅም አስመልክቶ በመቶኛ መረጃ መሞላት ያለበት ከመረጃ ሰጪው በመጠየቅ እንጂ በስሌት የሚሞላ አይደለም:: በክፍል 4.1 ዓምድ 8 ከዓምድ 13 ከተሞላው ጋር እኩል ከሆነ 100 ፐርሰንት እንደሆነ ያመለክታል::

## 4.3 በ2004 ዓ.ም. ፋብሪካው የተለያዩ አገልግሎቶችን በመስጠትና ከሌሎች ያገኘው ገቢዎች (በብር)፣

ዓምድ 2 - ፋብሪካው የማምረት አገልግሎት በመስጠት ያገኘው ገቢ፣ የሚመዘገበው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ደንበኞች ጥሬ ዕቃ አቅርበው የአገልግሎት ሥራ በመሥራት ያስከፈለ እንደሆነ ነው:: የጥገና ገቢ ከሆነ ግን በሚቀጥለው ዓምድ የሚካተት ስለሆነ ከዚህ ውስጥ አይገባም::

ዓምድ 3 - የማደስና የጥገና አገልግሎት ሥራ በመሥራት የተገኘ ገቢ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው ለደንበኞች የጥገና ሥራ በመሥራት ያገኘውን ገቢ ይመለከታል::

ዓምድ 4 - ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸው በተገዙበት ሁኔታ ተመልሰው ከተሸጡ ዕቃዎች የተገኘ ገቢ፣ ፋብሪካው ለምርት ተግባር ሊጠቀምበት ከጥናት ዓመቱ በፊትም ሆነ በጥናት ዓመቱ ውስጥ ከገዛው ዕቃ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ መልሶ ከሸጠ ከዚህ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ይመዘገባል::

ዓምድ 5 - ለፋብሪካው ግልጋሎት በፋብሪካው ሠራተኞች የተመረቱ ቋሚ ንብረቶች ዋጋ፣ በፋብሪካው ሠራተኞች ለፋብሪካው ጥቅም እንዲውል የተመረተው ቋሚ ንብረት ባስከተለው ወጭ የገንዘቡ መጠን ተተምኖ በዚህ ዓምድ ሥር ይመዘገባል:: ሌላው አማራጭ ደግሞ በድርጅቱ የሂሣብ መዝገብ ላይ ይህን በሚመለከት የተመዘገበ የገንዘብ መጠን ከለ የተጠቀሰዉን በመውሰድ ይሞላል::

ዓምድ 6 - ከወለድ የተገኘ፣ በፋብሪካው ስም ባንክ ከተቀመጠ ገንዘብ የተገኘ የወለድ ገቢ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ዓምድ 7 - ማሽኖችንና ሌሎች ቋሚ ዕቃዎችን በማከራየት የተገኘ ገቢ፣ የፋብሪካውን ቋሚ ንብረቶች ማሽኖችና የመሳሰሉትን በጥናት ዓመቱ ውስጥ በማከራየት የተገኘ ገቢ ካለ በዚህ ዓምድ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ይሞላል::

ዓምድ 8 - ከኢንሹራንስ የተገኘ ገቢ፣ ፋብሪካው ለቋሚ ንብረትም ሆነ ለሌላ (ከሕይወትና አካል ውጭ) ከገባው ኢንሹራንስ በጥናት ዓመቱ ውስጥ ያገኘው ገቢ ካለ በዚህ ዓምድ ይመዘገባል:: 8

ዓምድ 9 - ከመንግሥት ዕርዳታ የተገኘ ገቢ፣ ፋብሪካው በተለያዩ ምክንያት ከመንግሥት ያገኘው ድጎማ ካለ በዚህ ዓምድ ሥር ይመዘገባል::ነገር ግን መንግስት የሰጠዉን የመሬት ስጦታን አይመለከትም በሊዝ የተሰጣቸዉ ስለሆነ::

ዓምድ 10 - ሌሎች ገቢዎች፣ ከዓምድ 2 እስከ 9 ከተዘረዘሩት ገቢዎችና አገልግሎቶች ውጭ ሌሎች ገቢዎች ካሉ በዚህ ዓምድ ሥር ተጠቃለው መሞላት ይኖርባቸዋል::
ዓምድ 11 - ድምር፣ ከዓምድ 2 እስከ 10 ያሉትን በመደመር በዚህ ዓምድ ይሞላል::

## ክፍል 5 - በ2004 ዓ.ም የተከማቹ ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ፣ ጥሬ ዕቃ ግዢና የምርት ወጭ (በብር)

Stoke

### 5.1 በ2004 ዓ.ም. የተከማቹ ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ (በብር)

በፋብሪካው ባለቤትነት ተከማችተው የሚገኙትን ዕቃዎች በሙሉ ይመለከታል:: እነዚህን በሚመለከት ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በሂሣብ መዛግብት ላይ የተመለከቱት በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ይመዘገባሉ:: ለመሸጥ ተብሎ የተገዙ ዕቃዎችን ክምችት ይጨምራል:: ጥሬ ዕቃዎች፣ ነዳጅ፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች የመሳሰሉትን እንዲሁም በመሠራት ላይ የነበሩ ዕቃዎች እና ተሰርተው የወጡ ዕቃዎች ባስከተሉት ወጭ መሠረት ይተመናሉ:: ጠቅላላ የተከማቹ ዕቃዎች ዋጋ በዓምድ 3፣ 4 እና 5 በሚከተለው መንገድ ይሞላሉ::

1. ተሠርተው የወጡ ዕቃዎች፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በፋብሪካው ተመርተው ለሽያጭ የተዘጋጁ ምርቶች ግምታቸው በገንዘብ ሲተመን ስንት እንደነበረ በዓምድ 3 እና 4 ውስጥ ይመዘገባል::

2. በመሠራት ላይ የነበሩ ዕቃዎች፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በፋብሪካው በመሠራት ላይ የነበሩ ምርቶች ግምታቸው በገንዘብ ሲተመን ስንት እንደነበረ በዓምድ 3 እና 4 ይመዘገባል:: በፋብሪካው በመሠራት ላይ ያሉ ቋሚ ንብረቶች ለምሣሌ፣ ሕንፃዎችን፣ ሌሎች የኮንስትራክሽን ሥራዎችንና የመሳሰሉትን አይጨምርም::

3. ጥሬ ዕቃዎች፣ ነዳጅና ልዩ ልዩ ዕቃዎች፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በመጋዘን ተከማችቶ የነበረው የጥሬ ዕቃዎች፣ ነዳጅ፣ የጽሕፈት መሣሪያዎችና የመሳሰሉት በገንዘብ ሲተመን ግምታቸው ስንት እንደነበረ በዓምድ 3 እና 4 ይመዘገባል:: ንብረትነቱ የሌሎች ድርጅቶች ሆኖ



Financial Statement - Present Mamate

በፋብሪካው እጅ የሚገኙ ዕቃዎችን አይመለከትም:: ነገር ግን ንብረትነቱ የዚሁ ፋብሪካ ሆኖ በሌሎች ድርጅቶች የሚገኝ ዕቃ ዋጋ መመዝገብ ይኖርበታል:: በፋብሪካው በመሥራት ላይ ላሉ ሕንፃዎችና ለኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚያገለግሉ ዕቃዎች ክምችት ዋጋም መካተት ይገባዋል::

4. <u>በተገዙበት ሁኔታ የሚሸጡ ዕቃዎች</u>:- ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጀመሪያና መጨረሻ በተገዙበት ሁኔታ ተመልሰው የሚሸጡ ዕቃዎች ክምችት ድርጅቱ እንደነበረው ተጠይቆ ባስከተሉት ወጪ መሠረት ተተምኖ በዓምድ 3 እና 4 ይመዘገባሉ::

## 5.2 ክምችት ፣ጥሬ ዕቃ ግዢና የምርት ወጭ (በብር)

<u>አማካይ</u>:- ለጥሬ ዕቃዎች፣ በመሥራት ላይ ለነበሩ ዕቃዎች እንዲሁም ለተመረቱ ዕቃዎች በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ያለውን የገንዘብ መጠን በዓመቱ መጨረሻ ካለው የገንዘብ መጠን ጋር በመደመርና ለ2 በማካፈል አማካይ የገንዘብ መጠን ይገኛል:: ስለዚህ የተገኘው የገንዘብ መጠን በተራ ቁጥር 1 ፣2 እና 3 ላይ ባለው ዓምድ 3 ላይ ይሞላል::

<u>በዓመቱ ውስጥ</u> - በጥናት ዓመት ውስጥ ድርጅቱ የጥሬ ዕቃ ለመግዛት ያወጣው ወጭ በዚህ ዓምድ ውስጥ ይሞላል:: የጥሬ ዕቃ ወጭ ሲባል ቀጥታ ምርቱን ለማምረት በቀጥታ የተጠቀመው ጥሬ ዕቃን እንጂ ስቴሽነሪ፣ ነዳጅና ልዩ ልዩ መለዋወጫዎችን አይጨምርም ስለዚህ የተገኘው የገንዘብ መጠን በተራ ቁጥር 4 በዓምድ 5 ላይ ይሞላል::

<u>በዓመቱ መጨረሻ</u> - ድርጅቱ በጥናት ዓመቱ መጨረሻ ያለውን የምርት ወጭ በዚህ ዓምድ ላይ ይመዘገባል:: ይህ ማለት የሂሣብ ሪፖርት ለሚያዘጋጁ **(Beginning finished goods + Beginning GIP stock + Cost of manufacturing) – (Ending finished goods + Ending GIP) = Cost of Sales** ወይም **Cost of Goods Sold** ይሰጣል ይህም የገንዘብ መጠን በተራ ቁጥር 5 በዓምድ 4 ውስጥ ይሞላል::
የሂሣብ ሪፖርት ስሌለባቸው ግን ከመጠይቁ ላይ ከዚህ በታች ያሉትን ክፍሎች

3.1 ተራ ቁጥር 6 ዓምድ 16

3.2 ተራ ቁጥር 4 ዓምድ 6(የአስተዳደራዊ ወጪን አይጨምርም)፣ 7፣8 ና 9

6.1 ተራ ቁጥር 12 ዓምድ 11

6.2 ተራ ቁጥር 7 ዓምድ 13

6.4 ተራ ቁጥር 1 ዓምድ 4 (ኤክሳይዝ ታክስ)

7.1 ተራ ቁጥር 4 ዓምድ 6 በመውሰድና በመደመር ይሞላል።

## ክፍል 6- በ2004 ፋብሪካው የተጠቀመባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎች፣ መያዣዎችና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች እንዲሁም በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ ሊጠቀም የሚችለው ጠቅላላ የጥሬ ዕቃ ዋጋ

### 6.1 በ2004 ዓ.ም. የጥሬ ዕቃዎች ብዛትና ጠቅላላ ዋጋ፣ መለዋወጫዎችና መያዣዎች

ዓምድ 2 - ፋብሪካው የተጠቀመባቸው ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎችና መያዣዎች፦ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው ምርት ለማምረት የተጠቀመባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ ለፋብሪካው ቀላል/ወቅታዊ/አነስተኛ ጥገናና ለእድሳት ያዋላቸው መለዋወጫዎች /ለማሽነሪ/ ፣መያዣዎችና ማሸጊያዎች ይመዘገባሉ። እንደ ማሸጊያና መጠቅለያ የመሳሰሉት በአንድነት ተጠቃለው ዋጋቸው ብቻ ልዩ ልዩ ዕቃዎች በሚለው በተራ ቁጥር 11 አቅጣጫ መሞላት ይኖርበታል።

ዓምድ 3 - መስፈሪያ፣ በዓምድ 2 ለተዘረዘሩት ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች መስፈሪያቸው በየአቅጣጫቸው በዚህ ዓምድ ሥር ይመዘገባል። መስፈሪያው በሜትሪክ ሲስተም መለኪያ መሠረት መሞላት ይኖርበታል። ዝርዝር የመስፈሪያ አጠቃቀም ከዚህ አሞላል መመሪያ መጨረሻ ላይ ተያይዟል።

ዓምድ 4 እና 5 - የዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች ኮድ እና የመስፈሪያ ኮድ፣ ለቢሮ ሥራ ስለሆነ ክፍት ይተዋል።

ዓምድ 6 እና 7 - ከአገር ውስጥ፣ በዓምድ 2 ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች ውስጥ ከአገር ውስጥ የተሠሩትንና ፋብሪካው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ የተጠቀመባቸውን በዓምድ 6 ውስጥ በየአንጻራቸው ብዛታቸው ይመዘገባል። በዓምድ 6 ብዛታቸው ለተመዘገበው ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋቸው በዓምድ 7 ውስጥ ይመዘገባል። ጠቅላላ ዋጋ የግዥን ዋጋ፣ ለትራንስፖርት፣ ልዩ ልዩ ታክስና ለሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች የወጣውን ገንዘብ ይጨምራል።

ዓምድ 8 እና 9 - ከውጭ አገር፣ በዓምድ 2 ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች ውስጥ በእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃ አቅጣጫ በውጭ አገር የተሠሩና ፋብሪካው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ለተጠቀመባቸው ዋና ዋና ጥሬ ዕቃዎች በዓምድ 8 ውስጥ ብዛታቸው ይመዘገባል:: በዓምድ 9 ውስጥ በዓምድ 8 ብዛታቸው በተመዘገበላቸው አንጻር ጠቅላላ ዋጋቸው ይጻፋል:: ጠቅላላ ዋጋ የግዥን ዋጋ፣ ለትራንስፖርት፣ ለልዩ ልዩ ታክስና ለሌሎች ወጭዎች የወጣውን ገንዘብ ይጨምራል::

ዓምድ 10 እና 11 - ጠቅላላ ድምር፣ በዓምድ 6 እና 8 የተመዘገበው መጠን ለእያንዳንዱ ዕቃ በመደመር በዓምድ 10 ውስጥ ይመዘገባል:: እንዲሁም በዓምድ 7 እና 9 የተመዘገበውን እያንዳንዱን ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ በመደመር በዓምድ 11 ውስጥ ይመዘገባል::

ዓምድ 12 - ፋብሪካው በ2004 ዓ. ም. በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ ሊጠቀምበት የሚችለው የጥሬ ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ፣ ፋብሪካው በጥናት ዓመቱ ካለምንም ማቋረጥ በሙሉ ጉልበቱ ቢሠራ ሊያመርት የሚችለውን የምርት መጠን ለማምረት የሚያስፈልገው የጥሬ ዕቃ ጠቅላላ ዋጋ በዚህ ዓምድ ይሞላል:: የዚህ ዓምድ አሞላል ከላይ ለንዑስ ክፍል 6.1 ዓምድ 7 እና 9 ከተሰጠው ማብራሪያ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ በዚያው መሠረት መሞላት ይኖርበታል:: በዚህ ዓምድ የአገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጥሬ ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ተደምረው እንደሚመዘገቡ መገንዘብ ያስፈልጋል::

## 6.2 በ2004 ዓ.ም. ከምርት ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ላላቸው የተደረጉ ወጪዎች (በብር)

ዓምድ 3 ፣5እና 6፣ ፋብሪካው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት የተጠቀመባቸው ከባድ ጥቁር ናፍጣ፣ ጥቁር ናፍጣና ሌሎች ነዳጆች መስፈሪያቸውን በዓምድ 3 በመግለጽ ብዛትና ጠቅላላ ዋጋቸው በዓምድ 5 እና 6 በየአንፃራቸው ይመዘገባል:: ነገር ግን ፋብሪካው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ከተጠቀመው ኤሌክትሪክ እራሱ ላመነጨው የዋለውን የነዳጅ መጠን አይጨምርም:: ይህም ማለት ኤሌክትሪክ ለማመንጨት የዋለው የነዳጅ ዋጋ ከኤሌክትሪክ ፍጆታ ጋር ተደምሮ በሚቀጥለው ዓምድ መግባት ይገባዋል:: በዓምድ 6 የሚሞላው የነዳጅ ፍጆታ ለኃይል ማመንጫ (ለማሽኖች) የዋለውን ብቻ እንጂ ለትራንስፖርት የዋለው መግባት ያለበት ከትራንስፖርት ወጭ ጋር ተጠቃሎ በክፍል 6.3 በዓምድ 6 ውስጥ ነው::

ዓምድ 4. ለቢሮ ሥራ ስለሆነ ክፍት ይተዋል::

ዓምድ 7 - የኤሌክትሪክ ፍጆታ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው የተጠቀመበት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ወጪ በብር በዚህ ዓምድ ይመዘገባል:: የተጠቀመበት የኤሌክትሪክ ፍጆታ ለመብራት ኃይል ባለሥልጣን በተከፈለው መሠረት መወሰድ ሲገባው፣

ፋብሪካው ያመነጨው ግን ለማመንጨት ባስከተለው ወጭ መሠረት የገንዘቡ ልክ ይተመናል። ጠቅላላ ዋጋ መስጠት ያለበት ድርጅቱ ከገዛውና ካመረተው ላይ ለሌሎች ድርጅቶች የሸጠውን በመቀነስ ነው።

ዓምድ 8 ማገዶ፣ ድንጋይ ከሰል፣ ከሰልና ወዘተ... ለኃይል ማመንጫ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ለኃይል ማመንጫ የዋለው የማገዶ፣የድንጋይ ከሰል፣ የከሰል ወዘተ ጠቅላላ ዋጋ ይመዘገባል። ለግንባታ የዋለ የእንጨት ወጪ በዚህ ዓምድ መግባት እንደሌለበት መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 9 - ለአነስተኛ እድሳትና ጥገና ሥራ የተደረገ ወጪ ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ የፋብሪካውን ንብረት ማለትም የማምረቻ ህንጻዎች፣ ማሽኖችና የመሳሰሉትን ለጠገኑና ላደሱ ለሌሎች ድርጅቶች የተከፈለ ነው።

ዓምድ 10 - ለውኃ ፍጆታ ወጪ የተደረገ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው ለተጠቀመበት ውኃ የከፈለው ገንዘብ ይመዘገባል።

ዓምድ 11 - በተገዙበት ሁኔታ ለተሸጡ ዕቃዎች የተደረገ ወጪ፣ በፋብሪካው ተገዝተው ምንም ዓይነት ለውጥ ሳይደረግባቸው ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት የተሸጡ ዕቃዎች ሲገዙ ያስከተሉት የወጪ መጠን ይመዘገባል። ፋብሪካው ለምርት ተግባር ሊጠቀምበት ብሎ ገዝቶ የሸጠውን እንዲሁም ለመሸጥ ብሎ የገዛውን ዕቃ ያጠቃልላል።

ዓምድ 12 - ሌሎች ድርጅቶች ለሰጡት አገልግሎት የተከፈለ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው ለሌሎች ድርጅቶች የሚሠራውን ዕቃ በማቅረብ ድርጅቶቹ ለሰጡት አገልግሎት የተከፈለው በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 13 - ድምር፣ በዓምድ 6፣ 7፣ 8፣ 9፣ 10፣ 11 እና፣ 12 ሥር የተመዘገቡትን በአንድነት በመደመር በዓምድ 13 መሞላት አለበት።

## 6.3 በ2004 ዓ.ም. ከምርት ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ለሌላቸው ሥራዎች የተደረጉ ወጪዎች (በብር)

ዓምድ 2 - ፈቃድ ለማውጣትና እድሳት የተከፈለ፣ በጥናት ዓመቱ ውስጥ ለማምረቻ ኢንዱስትሪው ፈቃድ እደሳ ወይም ፈቃድ ለማውጣት ለተለያዩ የመንግሥት ድርጅቶች የተከፈለው በአንድነት ተጠቃሎ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 3 - ለማስታወቂያ፣ የፋብሪካውን ምርት ለማስተዋወቅ ወይም ለሌሎች ከዚህ ጋር ለተዛመዱ ጉዳዮች ሲባል የተለያዩ የብዙኃን መገናኛዎችን ወይም ሌላ አመች መንገድ በመጠቀም ለተደረጉ የቅስቀሳ ሥራዎች የተደረገ ወጪን ያጠቃልላል።

ዓምድ 4 - ለጽሕፈት መሣሪያ፣ ለፖስታ፣ ለቴሌፎን ፣ለኢንተርኔትና ለመሳሰሉት የተከፈለ፣ ፋብሪካው በጥናት ዓመቱ ውስጥ ለጽሕፈት መሣሪያ፣ ለፖስታ፣ ለቴሌፎን፣ለኢንተርኔት፣ ለፋክስና ለመሳሰሉት ያወጣውን በሙሉ በመደመር በዚህ ዓምድ ሥር መሞላት አለበት።

ዓምድ 5 - ለሂሣብ አጣሪዎች፣ ለሕግ አማካሪዎችና ለመሳሰሉት የተከፈለ፣ የፋብሪካውን ሂሣብ ለማስመርመር፣ ለሕግ ባለሙያዎች፣ ለቦርድ አባላትና ለመሳሰሉት በፋብሪካው ስም ወጪ የተደረገ በሙሉ በዚህ ዓምድ ይሞላል።

ዓምድ 6 - ለትራንስፖርት የተከፈለ (ለትራንስፖርት የዋለ ነዳጅን ይጨምራል)፣ በዚህ ዓምድ ሥር ለትራንስፖርት የሚውሉ መኪናዎች ኪራይ የተከፈለውንና የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ የድርጅቱ መኪናዎች የወጣውን ነዳጅ በአንድነት መመዝገብ ይኖርበታል።

ማስታወሻ፡- ይህ ዓምድ ለፋብሪካው ንብረት ለሆኑ መኪኖች በጥናቱ ዓመት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉትን የመኪና መለዋወጫዎች ወጪ ማካተት አለበት።

ዓምድ 7 - ለወለድ የተከፈለ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ፋብሪካው ከባንክ ወይም ከሌላ ገንዘብ ነክ ድርጅቶች ለተበደረው ገንዘብ የተከፈለውን ጠቅላላ የወለድ መጠን በዚህ ዓምድ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 8 - ለባንክ አገልግሎት የተከፈለ፣ በጥናት ዓመቱ ውስጥ ፋብሪካው ከባንክ ላገኘው አገልግሎት የከፈለውን የገንዘብ መጠን በዚህ ዓምድ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 9 - ማሽኖችንና ሌሎች ቋሚ ዕቃዎችን በመከራየት የተደረገ ወጪ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ከሌሎች ድርጅቶች ለፋብሪካው ሥራ የሚውሉ ማሽኖች፣ ሕንፃዎችን፣ ሌሎች ቋሚ ዕቃዎችን በመከራየት የተደረገውን ወጪ በአንድነት በመደመር በዓምዱ ማስገባት ያስፈልጋል።

ዓምድ 10 - ለንብረት ኢንሹራንስ የተከፈለ፣ ፋብሪካው ላሉት ቋሚ ንብረቶች የኢንሹራንስ ዋስትና በመግባት በጥናት ዓመቱ ያደረገው መዋጮ በዚህ ዓምድ መመዝገብ ይኖርበታል።

ዓምድ 11 - ለአሞርታይዜሽን የተደረገ ወጪ፣ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለጥሩ ስም፣ለቅድ መብት፣ለአዕምሮዊ ንብረት ወዘተ..... ያደረገው ወጪ ካለ በዚህ ዓምድ ይሞላል፡፡

ዓምድ 12 - ሌሎች ወጪዎች፣ በመጠይቁ ከዓምድ 2 እስከ 11 ከተጠቀሱት ውጪ የተደረገ ወጪ ካለ በዚህ ዓምድ ተጠቃሎ ይሞላል፡፡

ዓምድ 13 - ድምር፣ ከዓምድ 2 እስከ 12 ያሉትን በአንድነት በመደመር መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡

## 6.4 በ2004 ዓ.ም. ለልዩ ልዩ ታክሶች የተደረጉ ወጪዎች

15%

ዓምድ 2 - ለተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT የተከፈለ፣ በፍጆታ ዕቃ ወይም በተጠቃሚ ወጪ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ታክሱ የሚጣለውም በፍጆታ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ በጥናት ዓመቱ የተለያዩ የፋብሪካው ምርት በሚሸጥበት ወቅት ከደንበኞች የተሰበሰበ የተጨማሪ እእሴት ታክስ በሙሉ በዚህ ዓምድ ሥር ተጠቃሎ መግባት ይኖርበታል፡፡ ታክሱ ከምርትና ጥሬ ዕቃ አምራቾች ጀምሮ እስከ ቸርቻሪዎች ድረስ በሚደረጉ የማምረትና የማሰራጨት (የማከፋፈል) ሂደቶች በሁሉም ደረጃዎች በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ይሰበሰባል፡፡

10%

*ዓምድ 3 - ለተርን ኦቨር ታክስ የተከፈለ፦ በአገር ውስጥ በሚከናወን የምርት ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ወቅት በየደረጃው የሚጣል ታክስ ነው፡፡ ስለሆነም በጥናት ዓመቱ ለተርን ኦቨር (TOT) የከፈለው የገንዘብ መጠን በዚህ ውስጥ ይመዘገባል፡፡*

*ዓምድ 4 - ለኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ፣ በአገር ውስጥ በሚመረቱ እና በሚገቡ የተወሰኑ የ ቅንጦት ምርቶች/ዕቃዎች ላይ የሚጣል ታክስ ነው፡፡*

ኤክሳይዝ ታክስ ከሚከፈልባቸው ምርቶች ዋና ዋናዎቹ ስኳር፣ ለስላሳ መጠጦች፣ የታሸጉ ውሃዎች፣ አልኮል መጠጦች፣ ቢራ፣ ትምባሆ፣ ጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳና ሌጦ፣ የፕላስቲክ ወጤቶች ፣ ወርቅና ሌሎች ጌጣ ጌጦች ተጠቃሽ ናቸው፡፡
ፋብሪካው በጥናቱ ዓመት ላመረተው ምርት የከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን ተጠይቆ በዚህ ዓምድ በተሰጠው ባዶ ቦታ መሞላት ይኖርበታል፡፡



20165.

ዓምድ 5 - በትርፍ ላይ የተከፈለ የገቢ ታክስ፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው ባገኘው ትርፍ ላይ የተከፈለ የገቢ ታክስ ይመዘገባል።

ዓምድ 6 - ድምር፣ በዚህ ዓምድ ሥር በዓምድ 2፣ 3 እና 4 ውስጥ የተመዘገቡትን ቁጥሮች በመደመር መመዝገብ ያስፈልጋል።

## ክፍል 7 - የቋሚ ንብረትና የመዋዕለ ንዋይ ወጪ

### 7.1 በ2004 ዓ. ም.የፋብሪካው ቋሚ ንብረት ዓይነትና መዋዕለ ንዋይ (በብር)፣

ስለ ቋሚ ንብረት የተጠየቀው ከሂሣብ መዛግብትና ከሂሣብ ማመዛዘኛ በተገኘው ማስረጃ መሠረት ይሞላል:: ፋብሪካው የሚገለገልባቸው ከአንድ ዓመት በላይ የአገልግሎት ዕድሜ ያላቸው የፋብሪካው ቋሚ ንብረቶች ሁሉ ዋጋቸው በዚህ ውስጥ መገለጽ ይኖርበታል:: እነዚህም የፋብሪካው ንብረቶች የተገዙ፣ ከሌሎች ድርጅቶች የተወሰዱ ወይም ፋብሪካው ያሠራቸው ወይም ያመረታቸው ሊሆኑ ይችላሉ:: የማምረት ችሎታቸውን ለመጨመር ወይም ጥቅም የሚሰጡበትን ጊዜ ለማራዘም በቋሚ ንብረት ላይ ለተደረጉ ለውጦች፣ ለማሻሻያዎች፣ ለመጓጓዣና ለማስተከያ የወጣው ገንዘብ በዚህ ውስጥ መጨመር ይኖርበታል::

ዓምድ 2፣

1. መኖሪያ ቤት፣ የፋብሪካው የሆኑና ለፋብሪካው ሠራተኞች ለመኖሪያ ቤትነት የሚያገለግሉትን ይመለከታል::

2. መኖሪያ ያልሆኑ ቤቶች፣ የፋብሪካው ሕንፃዎች፣ መጋዘኖች፣ የቢሮ ሕንፃዎችና የሠራተኛ መመገቢያ ሕንፃዎች የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

3. ሌሎች የኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ መንገዶች፣ የመኪና መቆሚያ ቦታዎች፣ አጥር፣ ቦይ፣ በመሬት ላይ የተደረገ ለውጥ (መሬት መደልደል ወዘተ...) እና የመሳሰሉት በዚህ አርዕስት ሥር ይመደባል::

4. የማምረቻ መሣሪያዎችና ዕቃዎች (Machinery and Equipment):- ለኃይል ማመንጫ ለኢንዱስትሪና ለብረታ ብረት ሥራ፣ የሚያገለግሉትን ወዘተ... ያጠቃልላል::

5. ተሽከርካሪዎች፣ ሰውና ዕቃ ለማመላለስ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎችን ይመለከታል::

6. ሌሎች (የቢሮ፣ የቤት ዕቃዎችና የመሳሰሉት)፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ሶፋ፣ ማቀዝቀዣ፣ ሼልፍና የመሳሰሉት በዚህ አርዕስት ሥር ይመደባሉ::

ዓምድ 3 - በዓመቱ መጀመሪያ ያለው የዋጋ ግምት፣ ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጀመሪያ ላይ የፋብሪካው ቋሚ ንብረት የተጣራ የንብረት ዋጋ ስንት እንደነበረ በዓምድ 2 ለተጠቀሱት የቋሚ ንብረት ዓይነቶች በየአቅጣጫው በዓምድ 3 ውስጥ ይመዘገባል::

ዓምድ 4 - በዓመቱ ውስጥ ለቋሚ ንብረት መግዣና ለከባድ ጥገና ወጪ የሆነ፣ በዓምድ 2 ውስጥ ከተጠቀሱት የቋሚ ንብረት ዓይነቶች ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው የገዛው /አዲስ ወይም አሮጌ/ ቋሚ ንብረት ካለ በዓምድ 4 ውስጥ የገንዘቡ መጠን ይመዘገባል:: የማምረት ችሎታውን ለመጨመር ወይም ጥቅም የሚሰጥበትን ጊዜ ለማራዘም በቋሚ ንብረት ላይ የተደረጉ ለውጦች፣ ለማሻሻያዎች፣ ለማስገቢያና ለማስተካከያ የወጣው ገንዘብ በዚህ ውስጥ መጨመር ይኖርበታል:: ነገር ግን ለአነስተኛ እድሳትና ጥገና የወጣው ሂሣብ ከዚህ ጋር አይጨምርም::

ዓምድ 5 - በዓመቱ ውስጥ የተሸጡና ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ፣ ዓምድ 2 ውስጥ ከተጠቀሱት የቋሚ ንብረት ዓይነቶች ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ፋብሪካው የሸጠው ወይም ከአገልግሎት ውጭ የሆነ ንብረት ከነበረው በዓምድ 5 ውስጥ የገንዘቡ መጠን ይመዘገባል::

ዓምድ 6 - በዓመቱ የአገልግሎት ቅናሽ (Depreciation):- በዓምድ 2 ውስጥ ለተጠቀሱት የቋሚ ንብረት ዓይነቶች ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት ውስጥ ለአገልግሎት (እርጅና) ቅናሽ የታሰበው የገንዘብ መጠን በየአቅጣጫው ይመዘገባል:: ጥናቱ ከሚመለከተው ዓመት በፊት ታስቦ የነበረው ማለትም **የተጠራቀመ የአገልግሎት ቅናሽ ከዚህ ጋር መጨመር የለበትም**::

ዓምድ 7 - በዓመቱ መጨረሻ የተጣራ የንብረት ዋጋ፣ በዓምድ 2 ውስጥ ለተጠቀሱት የቋሚ ንብረት ዓይነቶች ጥናቱ በሚመለከተው ዓመት መጨረሻ የነበራቸው ዋጋ ስንት እንደነበረ በየአቅጣጫቸው ይመዘገባል:: ይህን ለማስላት በዓምድ 3 እና 4 የተመዘገበውን የገንዘብ መጠን በዓምድ 2 ውስጥ ለተዘረዘሩት ለእያንዳንዳቸው በመደመር ከተገኘው ላይ በዓምድ 5 እና 6 የተመዘገበውን የገንዘብ መጠን ደምሮ በመቀነስ ማግኘት ይቻላል:: ይኸውም፣

*ዓምድ 7 = (ዓምድ 3 + ዓምድ 4) - (ዓምድ 5 + ዓምድ 6)*

ማስታወሻ፣

1/ በመሠራት ላይ ያሉ ግንባታዎች (Construction in progress) በሚያጋጥምበት ወቅት የግንባታው ዓይነት ተጠይቆ በቋሚ ንብረቱ ዓይነት ተለይቶ መመዝገብ ይኖርበታል::

2/ ተገዝተው በመምጣት ላይ ያሉ ዕቃዎች (Goods in Transit) በሚያጋጥምበት ወቅት የቋሚ ንብረቱ ዓይነት ተጠይቆ በግልጽ በሚመለከተው አንፃር መመዝገብ አለበት::

## የሂሣብ ሪፖርት ለሌላቸው ድርጅቶች የአገልግሎት ቅናሽ (Depreciation) ስሌት መመሪያ

- ድርጅቶች ማለትም የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪ የበጀት ዓመታቸው የሚሰበሰው በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ሐምሌ 1 - ሰኔ 30 በሚለው ነው::
- ቋሚ ንብረቱ የተገዛው/የተሰራው፣ ከፍተኛ ጥገና የተደረገለት በሐምሌ ወር ውስጥ ከሆነ በዚህ የበጀት ዓመት የሙሉ ዓመት የአገልግሎት ቅናሽ ይሰላል:: ለምሳሌ ዕቃው የተገዛው በሐምሌ 1990 ከሆነ ይህ የበጀት ዓመት ማለት ከሐምሌ 1/1990 - ሰኔ 30/1991 ስለሆነ የ1991፣ 1992፣ 1993፣ 1994፣ 1995፣ 1996፣ 1997፣ 1998፣ 1999፣2000፣ 2001፣ 2002፣2003 ና 2004 የሙሉ ዓመት የአገልግሎት ቅናሽ ከተሰራ በኋላ በ2004 በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ያለው (Book Value) ወደ መጠይቁ ይመጣል::
- ቋሚ ንብረቱ የተገዛው/የተሰራው፣ ከፍተኛ ጥገና የተደረገለት ከበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ወር በኋላ ከሆነ ግን ከሚቀጥለው የበጀት ዓመት ጀምሮ የአገልግሎት ቅናሽ (Depreciation) ይሰላል::
- በመጠይቁ ላይ እንዲሞላ የሚፈለገው በ2004 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ያለው Book Value ስለሆነ ለእያንዳንዱ የቋሚ ንብረት ዓይነት (Category) ለየብቻው ስሌቱ ይካሄዳል:: በተጨማሪ ለአንድ አይነት የቋሚ ንብረትም ቢሆን ዕቃው ከተገዛ በኋላ ሌላ ተመሳሳይ ዕቃ በሌላ ዓመት ቢገዛ ወይም ከፍተኛ ጥገና ቢካሄድ ወይም ከአገልግሎት ውጭ ቢሆን ሁኔታው ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ /ማለትም ከላይ ያለውን ሕግ/ በመከተል ስሌቱ ለየብቻ ይካሄዳል::
- አንድ ቋሚ ንብረት ከጥናት ዓመቱ መጀመሪያ በፊት ቢገዛና ከጥናት ዓመት በፊት ከአገልግሎት ውጭ ከሆነ ይሄ እዚያው ስለሚያልቅለት ወደ መጠይቁ ክፍል አይመጣም::
- የማምረቻ መሣሪያዎችን በተመለከተ ሁሉም የአገልግሎት ቅናሽ የሚሰላው በ 20 % ነው::

➢ በጥናት ዓመቱ ውስጥ ከአገልግሎት ውጭ ለሆኑ፣ ለተሸጡ አዲስ ለተደረገ ኢንቨስትመንት ምንም ዓይነት የአገልግሎት ቅናሽ አይደረግም።

➢ በመጠይቁ ላይ በዓምድ 6 የሚሰላው የአገልግሎት ቅናሽ በዓምድ 3 ላይ ካለው የዓመቱ መጀመሪያ የዋጋ ግምት ነው።

<u>ምሳሌ 1</u>፡- አንድ ኬክ አምርቶ ለሚሸጥ ድርጅት የኬክ መጋገሪያ ማሽን በሐምሌ 15/2000 በ5,500 ብር ገዝቶ ነበር ቢባል

- የበጀት ዓመቱ ሐምሌ1/2000 - ሰኔ 30/2001
- የአገልግሎት ቅናሽ የሚሰላው ከ2001- 2003 ድረስ ነው ይኸውም ለሦስት ዓመት ይሆናል።

በ2004 መጀመሪያ ያለ ዋጋ

5500 x 0.512 = <u>2816</u> ብር ይሆናል

<u>ምሳሌ 2</u>፡- አንድ የዱቄት ፋብሪካ <u>በታህሳስ</u> 1995 ለፋብሪካው የሚሆን ቤት በ65,000 ብር ቢያሠራ፣ ማሽኑን በ12,000 ብር ገዛ ብንባል በታህሳስ 1995 የተገዙት ቋሚ ንብረቶች ከ ሐምሌ 1/1994 - ሰኔ 30/1995 ባለው በጀት ዓመት የሚታዩ ሆነው ዓመቱ ስለተጀመረ የአገልግሎት ቅናሽ አናሠላም

<u>ቤት</u>

1996 65,000 x 0.663= 43,095

1997 መኖሪያ ያልሆኑ ቤቶች ውስጥ በ2004 ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ይገባል

1998

1999 <u>ወፍጮ (ማሽን)</u>

2000 12,000 x 0.168 = 2,016

2001 የማምረቻ መሣሪያዎችና ዕቃዎች ውስጥ በ2004 ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ይገባል።

2002

2003

<u>ምሳሌ 3</u>፡- የቆዳ ውጤቶችን የሚያመርት ድርጅት በመስከረም 1986 አንድ በኤሌክትሪክ የሚሠራ የቆዳ ማለስለሻ በ50000 ብር እንዲሁም ደግሞ አንድ የቆዳ መፋቂያ መስከረም 1987 ዓ.ም በ35000 ብር ገዛ፡-

- በጥር 2002 ይኸው ድርጅት አንድ ተጨማሪ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ማለስለሻ በ3 ሚሊዮን ብር ገዛ፡-
- ድርጅቱ በመስከረም 1986 የገዛው የቆዳ ማለስለሻ በየካቲት 2002 ዓ.ም የገዛው ከአገልግሎት ውጭ ሆነ፡-

- በጥር 2002 የተገዛው የቆዳ ማለስለሻ በየካቲት 2004 ከፍተኛ ጥገና በ80000 ብር ተካሄደለት፡፡-
- በመስከረም 1987 የተገዛው የቆዳ መፋቂያ በሚያዚያ 2004 በ5000 ብር ተሸጠ፡፡-
- በየካቲት 2004 ዓ.ም የድርጅቱን ሥራ ይበልጥ ለማቀላጠፍ አንድ ኮምፒዩተር በ 10000 ብር ተገዛ፡-
- ጥቅምት 2004 ላይ ፕሪንተር በ 3000 ብር ተገዛ፡፡
- በ2005 ታህሳስ ወር ላይ ጥሬ ዕቃ ማስባሰቢያና ምርት ማሰራጫ አንድ ፒክ አፕ ተሽከርካሪ በ415000 ብር ተገዝቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡-

$3,000,000 \times 0.8$
$= 240,000$

$\Rightarrow 240,000 + 980$
$= 240,980$

$5000 - 980$
$= 4020$

$2400,980 \times 0.2$
$= 480,196$

investment $80,000 + 3,000 = 83,000$

(13)

1990 400,000

0.055

$400,000 \times 0.055$
$= 22,000$

$22,000 \times 0.2 = 4400$

$\Rightarrow 22,000 - 4,400$
$= 17600$

| ተራ ቁ. | ክንዋኔ | በኤሌክትሪክ የሚሰራ የቆዳ ማለስለሻ | የቆዳ መፋቂያ | የቆዳ ማለስለሻ | የቆዳ ማለስለሻ ከፍተኛ ጥገና | ኮምፒዉተር እና ፕሪንተር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቋሚ ንብረቱ የተገዛበት ከፍተኛ ጥገና የተደረገበት ዓመት | መስከረም 1986 | መስከረም 1987 | ጥር 2002 | የካቲት 2004 | የካቲት 2004(ኮምፒዉተር) ጥቅምት 2004(ፕሪንተር) |
| 2 | ቋሚ ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ | 50000 ብር | 35000 ብር | 3000000 ብር | 80000 ብር | 13000 ብር |
| 3 | ግዢው የሚውልበት የበጀት ዓመት | ሐምሌ 1/1985 - ሰኔ 30/ 1986 | ሐምሌ 1/ 1986 - ሰኔ 30/ 1987 | ሐምሌ1/2001 -ሰኔ 30/ 2002 | ሐምሌ 1/2003 - ሰኔ 30/ 2004 | ሐምሌ 1/2003 - ሰኔ 30/ 2004 |
| 4 | ከጥናት ዓመቱ በፊት ከአገልግሎት ውጭ የሆነ እስ | የካቲት 2002 | ሚያዝያ 2004 | የለም | የለም | የለም |
| 5 | የአገልግሎት ቅናሽ የሚሰላበት ዓመታት | 1987- 2001 | 1988 - 2003 | 2003 | የለም(አይደረግ ለትም) | የለም(አይደረግ ለትም) |
| 6 | የአገልግሎት ቅናሹ ዓመት ብዛት | 15 ዓመታት እላፊ አለው | 16 ዓመታት | 1 ዓመታት | - | - |
| 7 | ማባገሮው | 0.035 | 0.028 | ~~0.2~~ 0.8 | - | - |
| 8 | BIV ዕቃው ሲሸጥ ወይም dispose ሲሆን | *1750 | - | - | - | - |
| 9 | በ2004 ዓ.ም መጀመሪያ ያለው BIV | - | 980 | ~~600000~~ 2,400,000 | | |
| | | | ~~600980~~ 2,400,980 | | 80000 | 13000 |

* ይሄ ቋሚ ንብረት ከጥናት ዓመቱ በፊት ከአገልግሎት ውጭ ስለሆነ እዚህ ላይ ያበቃለታል::
* በተለያዩ ጊዜ የተገዙት የቆዳ ማለስለሻና የቆዳ መፋቂያ እንዲሁም የተካሄደው ከፍተኛ ጥገና ሁሉም የማምረቻ መሣሪያዎችና ዕቃዎችን የሚመለከቱ ስለሆነ ድምራቸው /600980/ ብር ወደ ዓምድ 2 ይተላለፋል::

የኮምፒዉተር እና ፕሪንተር ደግሞ በተ.ቁ 4 ዓምድ 4 ላይ ይመዘገባል::



[illegible]

## በ2004 ዓ.ም የማምረቻ/አገልግሎት ሰጭ ድርጅቱ ቋሚ ንብረትና መዋዕለ ንዋይ

| ተ.ቁ | የቋሚ ንብረቱ ዓይነት | በዓመቱ መጀመሪያ ያለው የዋጋ ግምት | በዓመቱ ውስጥ ለቋሚ ንብረቱ ወጪ የሆነ | በዓመቱ ውስጥ የተሸጠና ከአገልግሎት ውጪ የሆነ | በዓመቱ ግምታዊ የአገልግሎት ቅናሽ | በዓመቱ መጨረሻ የተጣራ የንብረት ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 1 | መኖሪያ ያልሆኑ ቤቶች | - | - | - | - | - |
| 2 | ማምረቻ መሣሪያዎችና ዕቃዎች | 600980 | 80000 | 980 | 120196 | 559804 |
| 3 | ተሽከርካሪዎች | - | - | - | - | - |
| 4 | ሌሎች የቢሮ ዕቃዎችና የመሳሰሉ | | 13000 | - | - | 13000 |
| 5 | ድምር | 600980 | 93000 | 980 | 120196 | 572804 |

በመስከረም 1987 የተገዛው የቆዳ መፋቂያ በሚያዚያ 2004 ዓ.ም በ5000 ብር ተሸጠ:: የተሸጠበት ዋጋ 5000 ብር በ2004 መጀመሪያ የነበረው BIV 980 ብር ነበር:: ይሄ በቋሚ ንብረት ላይ የተገኘ የ4020 ብር ትርፍ በ4.3 ሌሎች ገቢዎች በሚለው ዓምድ ላይ ይሞላል::

<u>ልዩነት</u>

* በዚህ ስሌት ምንም እንኳን ከሐምሌ እስከ ሚያዚያ ድረስ ላለው 9 ወር በ120196 ብር ላይ የአገልግሎት ቅናሽ ከተሰላ በኋላ ለቀሪው (120196 - 980) = 119216 ለ 4 ወር የአገልግሎት ቅናሽ መሰላት ቢኖርበትም ስሌቱን ላለማወሳሰብ የሙሉ ዓመት ብቻ ተወስዷል::

## 7.2 በዓመቱ ውስጥ ለቋሚ ንብረትና ሥራ ማስኬጃ የተደረገ ወጪ በምንጭ

ይህ ንዑስ ክፍል ፋብሪካው በጥናት ዓመቱ ውስጥ ለቋሚ ንብረትና ለሥራ ማስኬጃ ያደረገውን ወጪ ምንጩ ከየት እንደነበረ የሚመዘገብበት ነው:: ፋብሪካው በዓመቱ ውስጥ ያደረገው የቋሚ ንብረትና የሥራ ማስኬጃ ወጪ ያገኘው ከአገር ውስጥ ከሆነ ከድርጅቱ ገቢ፣ ከባንክ ብድር ወይም ከሌላ መሆኑ በተናጠል መጠየቅ ይኖርበታል:: ስለሆነም ከተራ ቁጥር 2-4 የተዘረዘሩት ሲደመሩ ጠቅላላ ከአገር ውስጥ ከተገኘው የገንዘብ ምንጭ ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 3 - ለቋሚ ንብረት፣</u> በንዑስ ክፍል 7.1 ዓምድ 4 ውስጥ የተመዘገበውን ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ፋብሪካው ከየት ለማግኘት እንደቻለ በንዑስ ክፍል 7.2 በዓምድ 2 በተጠቀሱት የገንዘብ ምንጭ አንፃር የገንዘቡ መጠን በዓምድ 3 ውስጥ ይመዘገባል:: ስለዚህ በንዑስ ክፍል 7.2 በዓምድ 3 የተዘረዘሩት ጠቅላላ ድምር በንዑስ ክፍል 7.1 በዓምድ 4 ከተዘረዘሩት ድምር ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል::

<u>ዓምድ 4 - ለሥራ ማስኬጃ፣</u> የሥራ ማስኬጃ ዋንኛ ትርጉሙ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚገኙ ሃብቶችና (current assets) በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሚከፈሉ ዕዳዎች (current liabilities) መሃከል ያለ ግንኙነት ነው::ይኸውም በአንድ አመት ጊዜ የሚከፈሉ ዕዳዎች ( current liabilities) ለምሳሌ የአጭር ጊዜ ብድር፣ የባንክ ኦቨርድራፍትና የንግድ ዕዳዎች በአንድ ዓመት ለሚገኙ ሃብቶች (current assets) ስቶኮች፣ ተከፋዮችና ጥሬ ገንዘብ የገንዘብ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ::ይሁን እንጂ ከተጨባጭ መረጃ አሰባሰብ አንጻር እነዚህን መረጃዎች ለሁሉም ድርጅቶች ማግኘት ስለማይቻል የሚቀጥለውን ዘዴ በመጠቀም የሥራ ማስኬጃን ማገኘት ይቻላል፡- ይህም በጥናት ዓመቱ ውስጥ ለቋሚ፣ ለጊዚያዊና ለኮንትራት ሠራተኞች ደመወዝና ለሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች የወጣ ወጪ፣ ፋብሪካው ለተጠቀመባቸው ጥሬ ዕቃዎችና መለዋወጫዎች መግዣ የወጣ ወጪ፣ ከምርት ሥራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ላላቸው እንደ ~~ኤሌክትሪክ፣ ማገዶ፣ ጥገና... ወዘተ~~ የተደረገ ወጪ እንዲሁም ለኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ ወጭ ነው::

<u>የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት (Long term investment)</u> የመሥራት ማለት ቋሚ ንብረትን ለመግዛት እንዲሁም የቋም ንብረትን ዕድሜ ለማራዘምና የመሥራት አቅሙን ለማሻሻል ተብሎ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው::ለዚህ የሚሆነው የገንዘብ ምንጭ የሚገኘው ከድርጅቱ ካፒታልና ከረጅም ጊዜ ብድር ነው::ይሁን እንጂ ድርጅቶቹ አዋጭ የሆነውን የካፒታል ድብልቅ (optimum capital stracture) በመጠቀም ለረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንትና ለሥራ ማስኬጃ የገንዘብ ምንጮቻቸው ሊጠቀሙ ይችላሉ::

በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ወጭዎች ለማውጣት ድርጅቱ የገንዘብ ምንጩ ምን ነበር የሚል ይሆናል::

ተ.ቁ.1 - ከሀገር ውስጥ፣ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ወጪ ከድርጅቱ ገቢ፣ ከባንክ ብድር፣ ከሌላ ከሆነ በዚህ ዓምድ ላይ የተራ ቁጥር 2፣ 3፣ 4 ድምር ይመዘገባል::

ተ.ቁ.2 - ከድርጅቱ ገቢ፣ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ገንዘብ የተገኘው ከድርጅቱ ገቢ ከሆነ በዚህ ዓምድ ላይ ይመዘገባል::

ተ.ቁ.3 - ከባንክ ብድር፣ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለሥራ ማስኪጃ ያወጣው ከባንክ የአጭር ጊዜ ብድር ወስዶ ከሆነ በዚህ ዓምድ ላይ ይመዘገባል::በረዥም ጊዜ የተገኘው ብድር ግን በሥራ ማስኬጃነት አይካተትም:: ምናልባት የረጅም ጊዜ ብድሩ ሲወሰድ ከፊሉ ለሥራ ማስኬጃነት ብድሩ በተወሰደበት ዓመት ሊታይ ይችላል::

ተ.ቁ.4 - ከሌላ፣ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ገንዘብ የተገኘው ከሌላ ምንጭ ከሆነ በዚህ ዓምድ ላይ ይመዘገባል::

ተ.ቁ.5 - ከውጭ ሀገር፣ ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ገንዘብ የተገኘ ው ከውጭ ሀገር ከሆነ በዚህ ዓምድ ላይ ይመዘገባል::

ተ.ቁ.6 - ጠቅላላ ድምር፣ ድርጅቱ ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ገንዘብ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ከሆነ የተራ ቁጥር 1 እና 5 ድምር ጠቅላላ ድምር ላይ ይመዘገባል:: ድርጅቱ ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ከሀገር ውስጥ ብቻ ከሆነ በተራ ቁጥር 1 ላይ የተመዘገበው የገንዘብ መጠን ወደ ጠቅላላ ድምር ይተላለፋል:: በመጨረሻም ድርጅቱ ለሥራ ማስኬጃ ያወጣው ወጪ ከውጭ ሀገር ብቻ ከሆነ ተራ ቁጥር 5 ላይ የተመዘገበው የገንዘብ መጠን ወደ ጠቅላላ ድምር ይተላለፋል::

ማስታወሻ፡-

ከትርፍ በኋላ የተከፈለ ግብር ገንዘብ እንደ ጥናት ዓመቱ ወጭዎች ስለማይቆጠሩ መመዝገብ የለባቸውም::

4.1

## ክፍል 8 - በ2004 ዓ.ም. ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ስላለመሥራቱና ሌሎች ያጋጠሙ ልዩ ልዩ ችግሮች

### 8.1 ፋብሪካው በሙሉ ጉልበቱ ካልሠራ ያልሠራበት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ምን እንደነበሩ ይገለጽ፡-

ፋብሪካው በጥናት ዓመቱ ውስጥ በሙሉ ጉልበቱ ካልሠራ (በ4.1 በተገኘው ምላሽ መሠረት የተሞላው ከ100 ፐርሰንት በታች ከሆነ) ለምን ሊሠራ እንዳልቻለ ሦስቱ ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ ተጠይቆ ከተገኙት መልሶች ጋር የሚዛመዱት ኮዶች ይከበቡና የመጀመሪያው ዋና ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 1፣ የሁለተኛው ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 2፣ እንዲሁም የሦስተኛው ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 3 ውስጥ ይጻፋል። በተቻለ መጠን ዋናዎቹ ችግሮች ከፋብሪካው ባለቤት ወይም ወኪል እንዲገለጽ ማድረግ እንጂ የተዘጋጁትን አማራጭ መልሶች አስቀድሞ መዘርዘሩ የሚገኘውን መልስ የተዛባ ሊያደርገው ይችላል። አማራጭ መልሶቹም።

| | |
|---|---|
| የጥሬ ዕቃዎች እጥረት ---------------- | =1 |
| የመለዋወጫ እጥረት ---------------- | =2 |
| የገበያ እጦት ---------------------- | =3 |
| የሥራ ማስኬጃ እጥረት ---------------- | =4 |
| ተደጋጋሚ የመሣሪያ ብልሽት ----------- | =5 |
| ከሠራተኞች ጋር ያሉ ችግሮች --------- | =6 |
| የመንግሥት ሕጎችና ደንቦች ጫና ----- | =7 |
| የመብራት እጥረት-------------------- | =8 |
| ሌላ /ይገለጽ/ ---------------------- | =9 |

### 8.2 ለጥያቄ 8.1 መልሱ ኮድ 3 ወይም የገበያ እጦት ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

የማምረቻ ድርጅቱ ከላይ ለጥያቄ 8.1 ከተሰጠው መልስ መሀከል ኮድ 3 ወይም የገበያ እጦትን የሚያካትት ከሆነ ለዚህ የገበያ እጦት ዋና ምክንያቱ ምን እንደሆነ ተጠይቆ የሚሰጠው መልስ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ጋር በማዛመድ የትክክለኛው መልስ ኮድ ከተከበበ በኋላ ኮዱ በተሰጠው የኮድ መጻፊያ ቦታ ይሞላል።

አማራጭ መልሶቹም:-

በጥራት ለመወዳደር አለመቻል ------------------- =1

በዋጋ ለመወዳደር አለመቻል -------------------- =2

ምርትን በማስተዋወቅ ለመወዳደር አለመቻል----- =3

ምርትን በማሰራጨት ለመወዳደር አለመቻል ---- =4

ሌላ ይገለጽ ------------------------------------ =5

**8.3 ለጥያቄ 8.1 መልሱ ኮድ 4 /የሥራ ማስኬጃ እጥረት/ ከሆነ የማምረቻ ኢንዱስትሪው የሥራ ማስኬጃ እጥረትን ለመቅረፍ ከብድር ሰጪ ተቋማት ብድር ለማግኘት ሞክሮ ነበርን?**

የማምረቻ ኢንዱስትሪው በጥያቄ 8.1 ከሰጣቸው መልሶች መካከል ኮድ 4 ወይም የሥራ ማስኬጃ እጥረት አንዱ ምክንያት ከነበረ ከብድር ሰጪ ተቋማት ብድር ለማግኘት የተሞከረ ወይም ያልተሞከረ መሆኑን በመጠየቅ የተገኘው መልስ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ኮድ 2 ተከቦ ትክክለኛ ኮዱ በተሰጠው የኮድ መስጫ ሳጥን ውስጥ መሞላት ይኖርበታል::

**8.4 ለጥያቄ 8.3 መልሱ ኮድ 1 ወይም አዎን ሆኖ የሥራ ማስኬጃ እጥረቱ ካልተወገደ ያልተቀረፈበት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?**

በጥያቄ 8.3 መልሱ ኮድ 1 ወይም አዎን ሆኖ ድርጅቱ የሥራ ማስኬጃ ካልተወገደ እጥረቱ ሊቃለል ያልቻለበት ምክንያት ተጠይቆ የተሰጠውን መልስ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ከተዛመዱ በኋላ ትክክለኛው ኮድ ተከቦ የኮድ ቁጥሩ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

አማራጭ መልሶቹም:-

የተፈቀደው የብድር መጠን በቂ ባለመሆኑ --------- =1

የብድር መመዘኛን ለማሟላት ባለመቻል ------------ =2

የወለዱ መጠን ከፍተኛ በመሆኑ ------------------ =3

የብድር መመለሻው ጊዜ አጭር በመሆኑ ----------- =4

የብድር ተቋማት አሠራር ቀልጣፋ ባለመሆኑ

/ረዥም ጊዜ በመውሰዱ/ -------------------------- =5

ሌላ /ይገለጽ/ ------------------------------------- =6

## 8.5 ፋብሪካው በአሁኑ ጊዜ (currently) ሥራውን ለማከናወን ያጋጠሙት ሦስት ዋና ዋና ችግሮች ምንድን ናቸው?

ፋብሪካው በአሁኑ ጊዜ ሥራውን በመሥራት ላይ እያለ ካጋጠሙት ችግሮች መካከል ዋና ዋና የሆኑት ሦስቱ ምን ምን እንደሆኑ ተጠይቆ ከተገኙት መልሶች ጋር የሚዛመዱት ኮዶች ይከበቡና የመጀመሪያው ዋና ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 7፣ የሁለተኛ ው ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 8፣ እንዲሁም የሦስተኛው ምክንያት ኮድ በካርድ ኮለም 9 ውስጥ ይጻፋል:: ለዚህ ጥያቄም በተቻለ መጠን ዋናዎቹ ችግሮች ከፋብሪካው ባለቤት ወይ ከሥራ አስኪያጁ እንዲገለጽ ማድረግ እንጂ የተዘጋጁትን አማራጭ መልሶች ለባለቤቱ አስቀድሞ መዘርዘሩ የሚገኘውን መልስ የተዛባ ሊያደርገው ይችላል::

አማራጭ መልሶቹም፣

- የጥሬ ዕቃዎች እጥረት ---------- =1
- የመለዋወጫዎች እጥረት -------- =2
- የገበያ እጦት ---------------- =3
- የሥራ ማስኬጃ /የገንዘብ እጥረት/ - =4
- ተደጋጋሚ የመሣሪያ ብልሽት ----- =5
- የሥራ ቦታ ምቹ አለመሆን ------ =6
- ከሠራተኞች ጋር ያሉ ችግሮች------ =7
- የመንግሥት ሕጎችና ደንቦች ጫና-- =8
- የመብራት እጥረት-------------- =9
- ምንም ችግር የለብኝም --------- = 10
- ሌላ /ይገለጽ/ ------------------ =11

## 8.6 ፋብሪካው ምርቱን ወደ ውጭ የሚልክ ከሆነ ያጋጠመው ችግር አለ?

ፋብሪካው ምርቱን ወደውጭ በሚልክበት ወቅት ችግር አጋጥሞት እንደሆነ ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1፣ የለም ከሆነ ደግሞ ኮድ 2፣ ከተከበበ በኋላ ትክክለኛ ኮዱ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::ነገር ግን ፋብሪከዉ ምርቱን ወደ ዉጭ የማይልክ ከሆነ በሰረዝ ይታለፋል::

**8.7 ለጥያቄ 8.6 መልሱ ኮድ 1 ወይም አዎ ከሆነ ፋብሪካው ምርቱን ወደ ውጪ ለመላክ ካጋጠመው ችግሮች መካከል ሦስቱን ዋና ዋና ችግሮች እንደ ቅደም ተከተላቸው ይገለጽ፣**

የማምረቻ ኢንዱስትሪው ለጥያቄ 8.6 የሰጠው መልስ ኮድ 1 ወይም አዎን ከሆነ ምርቱን ወደ ውጭ በሚልክበት ወቅት ያጋጠሙትን ሦስት ዋነኛ ምክንያቶች በመጠየቅ እንደ ቅደም ተከተላቸው በተሰጠው ባዶ ቦታ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ ለእዚህ ጥያቄ በካርድ ኮለሞች ላይ ምንም አይጻፍም፡፡

**8.8 ማምረቻ ኢንዱስትሪው የሚጠቀመው ጥሬ ዕቃ የውጭ ሀገር ከሆነ /በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ/ ዋና ምክንያቱ ምንድን ነው?**

ይህ ጥያቄ እየተሞላለት ያለው የማምረቻ ኢንዱስትሪ ምርቶቹን ለማምረት በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ የውጭ ሀገር ጥሬ ዕቃ የሚጠቀም ከሆነ አንድ ዋና ምክንያት ተጠይቆ በተሰጠው ካርድ ኮለም መሞላት ይኖርበታል፡፡ የውጪ ጥሬ ዕቃ ሲባል ማምረቻ ኢንዱስትሪው በቀጥታ ከውጪ ሀገር ያስመጣው ወይም የጥሬ ዕቃ ስሪቱ የውጪ ሀገር ሆኖ ማምረቻ ኢንዱስትሪው በሀገር ውስጥ ገበያ ላይ የገዛው ወይም ያገኘው ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በክፍል 6.1 ዓምድ 8 እና 9 ለተሞላላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ICT አጠቃቀም ቅጽ አሞላል መመሪያ

ይህ ቅጽ በጥናቱ የሚሸፈኑ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች በጥናቱ ዓመት የInformation & Communication Technology (ICT) ሁኔታቸው ምን ይመስል እንደነበር ለማወቅ የሚረዳ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ነው፡፡ በቅጹ ላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች መረጃ ሰጭውን በአግባቡ በመጠየቅ ትክክለኛውን መልስ ለማግኘትና በቅጹ ላይ ለመሙላት በዚህ ማብራሪያ የተሰጡትን ጽንሰ-ሀሳቦችና ፍችዎቻቸውን እንዲሁም የአሞላል መመሪያውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

### ጽንሰ-ሀሳብና ፍችዎቻቸው

ኮምፒዩተር - ማለት በተዘጋጀለት ፕሮግራም/ትዕዛዝ/ መሠረት የተለያዩ መረጃዎችን (ዳታ) የሚያቀነባብር/የሚያዘጋጅ/ የሚያሰላ መሣሪያ ነው፡፡

- ኮምፒዩተር በእጅ የሚያዝ/በጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ ወይም ከእነዚህ ያነሰና የበለጠ ሊሆን ይችላል፡፡

- በውስጣቸው ካልኩሌተር የያዙትን እንደ ሞባይል፣ ስልክ፣ ቴሌቪዥን የመሳሰሉትንና በኮምፒውተር የሚመሩትን መሣሪያዎች አይጨምርም፡፡

- ኮምፒዩተርን ከካልኩሌተር የሚለየው ባህርይ የተለያዩ ፕሮግራሞችን/ትዕዛዞችን ተቀብሎ ሥራ ማከናወኑና የተሰጠውንና የሠራውን ሥራ ውጤትም ጠበቆ ማቆየቱ ነው፡፡

Local Area Network - ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ (በቤት፣ በት/ቤት፣ በመሥሪያ ቤት፣ በኮምፒዩተር ላብራቶሪ፣ በፋብሪካ፣ ወዘተ...) የሚገኙ ኮምፒዩተሮች ወይም መሰል መሣሪያዎች (ለምሣሌ ፕሪንተር) የእርስ በርስ ትስስር/የግንኙነት መረብ ነው፡፡ ይህ ትስስር መረጃን በፍጥነት ከማስተላለፋም በላይ የቴሌፎን መስመር ሳያስፈልገው ሊዘረጋ ይችላል፡፡ ይህ የግንኙነት መረብ በአንድ ቦታ ወይም በተቀራረቡ ቦታዎች ያሉትን የአንድ ድርጅት ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎችን ኮምፒዩተሮች በማገናኘት መረጃና አንዳንድ የሥራ መሣሪያዎችን (ፕሪንተር) እንዲጋሩ ለማድረግ ያስችላል፡፡

International Net work

ኢንተርኔት - ማለት በየትኛውም ቦታ ያሉን ሰዎች በተለያየ መስመር/ቻናል መረጃ ለመለዋወጥ የሚያስችል የኮምፒዩተሮች ዓለም አቀፍ የግንኙነት መረብ ነው።

- ከኢንተርኔት የተገናኘ ኮምፒዩተር የተለያዩ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘትና መጠቀም ከራሱም ወደ ሌሎች መላክ ይችላል።

Website (ድረ-ገጽ) - ማለት የኤልክትሮኒክ ዶኪዩመንት/መረጃ (ምስሎች፣ ቪዲዮና የመሳሰሉት ዲጂታል ነገሮች) ክምችት/ስብስብ ሆኖ ከኢንተርኔት ጋር በተገናኘ ኮምፒዩተር የሚስተናገድና ከሌላ ወገን ጋር ለመገናኘት የሚያስችል ነው።

ICT - ማለት ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማለት ሲሆን፣ ማንኛውንም መረጃ በኤልክትሮኒክና ዲጂታል ዘዴ የሚቀበል፣ የሚልክ የሚያስቀምጥ (የሚያከማች)፣ የሚያቀነባብርና በተፈለገ ጊዜ የሚያቀርብ እንደ ኮምፒዩተር (pc)፣ ዲጂታል ቴሌቪዥንና ሮቦት የመሳሰሉትን መሣሪያዎችና ተግባራቸውንም ያካትታል።

ኮሙኒኬሽን - ማለት መረጃን፣ ሀሳብን አስተሳሰብን፣ አመለካከትንና የመሣሳሰሉትን ከአንድ ሰው ወደ ሌላ በንግግር፣ በጽሑፍና በምልክት ማስተላለፍ ነው።

ቴክኖሎጂ - ማለት ስለተለያዩ መሣሪያዎችና ሙያዎች (ጥበብ) ባህሪና አጠቃቀማቸው እንዲሁም በእነኚህ አማካኝነት ሰው አካባቢውን እንዴት መለወጥና መቆጣጠር እንደቻለ ያለን ግንዛቤ(እውቀት) ነው።

መሠረተ ልማት - ማለት ኅብረተሰብ/ድርጅት ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልጉት መሠረታዊ አገልግሎቶች(ኤልክትሪክ፣ ስልክ፣ ውሃ፣ መንገድና የመሳሰሉት) ናቸው።

ሠራተኛ - ማለት በድርጅቱ ተቀጥረው የሚሠሩትና የድርጅቶች ባለቤቶች ወይም ሸሪኮች ሆነው የሚሠሩትን ሁሉ ነው።

## ክፍል 9 - ስለ ድርጅቱ ICT አጠቃቀም መረጃዎች

ጥያቄ 1 - በጥናቱ የሚሸፈነው ድርጅት በጥናት ዓመቱ ኮምፒዩተር መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ኮድ 2 በመልስ (ኮድ) መስጫ ቦታው ዓምድ 3 ላይ ይሞላል::

ጥያቄ 2 - የጥያቄ 1 መልሱ ኮድ 1 ከሆነ ድርጅቱ በጥናት ዓመቱ ስንት ኮምፒዩተሮች እንደነበሩት ተጠይቆ ብዛታቸው በዓምዱ ይሞላል:: የሚመዘገበው የኮምፒዩተሮች ብዛት የሚሠሩትን ብቻ በመቁጠር ይሆናል::

ጥያቄ 3 - ድርጅቱ በጥናቱ ዓመት ሁለትና ከዚያ በላይ ኮምፒዩተሮች ከነበሩት እነዚህ ኮምፒዩተሮች እርስ በርስ መተሳሰራቸው/በግንኙነት መረብ መያያዛቸው (Local Area Network ያላቸው መሆኑ) ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ኮድ 2 በዓምድ 3 ይሞላል::

ጥያቄ 4 - በጥናት ዓመቱ ስንት የድርጅቱ ሠራተኞች በሥራ ላይ ኮምፒውተር አዘውትረው እንደተጠቀሙ ተጠይቆ ብዛታቸው በመቶኛ (ፐርሰንት) በዓምድ 3 ይፃፋል::

ጥያቄ 5 - በጥናቱ ዓመት ድርጅቱ ኢንተርኔት መጠቀም አለመጠቀሙ ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ኮድ 2 በዓምድ 3 ይሞላል::

ጥያቄ 6 - የጥያቄ 5 መልሱ ኮድ 1 ከሆነ በጥናቱ ዓመት ስንት የድርጅቱ ሠራተኞች በሥራ ላይ ኢንተርኔት አዘውትረው እንደተጠቀሙ ተጠይቆ ብዛታቸው በዓምድ 3 በመቶኛ (ፐርሰንት) ይሞላል::

ጥያቄ 7 - የጥያቄ 5 መልሱ አዎን ከሆነ በጥናቱ ዓመት ድርጅቱ ኢንተርኔት በአብዛኛው የተጠቀመው ለምን እንደሆነ ተጠይቆ ግዥ ለመፈጸም ከሆነ ኮድ 1 ምርቱን ለመሸጥ ከሆነ ኮድ 2 ለማስታወቂያ (Advertisement) ከሆነ ኮድ 3 ለድርጅቱ የውስጥ ሥራ ከሆነ ኮድ 4 ከሌሎች ድርጅቶች ጋር መረጃ ለመለዋወጥ ከሆነ ኮድ 5 ከመንግስት ድርጅቶች መረጃ ለማግኘት ከሆነ ኮድ 6 ለደንበኞች ሌላ አገልግሎት ለመስጠት ከሆነ ኮድ 7 ክፍያ ለመፈጸም ከሆነ ኮድ 8 e-mail ለመለዋወጥ ከሆነ ኮድ 9 በኢንተርኔት በኩል ስልክ ለመደወል ከሆነ (Telephoning over the

internet) ኮድ 10 በቅጽበት መልዕክት ስመስዋወጥ (Instant messaging) ከሆነ ኮድ 11 ኢንተርኔቱን ምንም ካልተጠቀመበት ደግሞ ኮድ 12 በዓምድ 3 ይሞላል፡፡

ጥያቄ 8 - የጥያቄ 5 መልሱ የለም ከሆነ ድርጅቱ ኢንተርኔት ያልተጠቀመበትን እንደ ዋና ምክንያት ተጠይቆ መልሱ በግንባር ጉዳይን ስመጨረስ ስለፈለገ ከሆነ ኮድ 1 የገንዘብ ችግር ከሆነ ኮድ 2 የመሠረተ ልማት ችግር ከሆነ ኮድ 3 የሠለጠነ ባለሙያ አለመኖር ከሆነ ኮድ 4 ኢንተርኔት ለድርጅቱ ምንም ጥቅም ስለማይሰጥ ከሆነ ኮድ 5 ከላይ ከተዘረዘሩት ሌላ ምክንያት ከሆነ ተገልጾ ኮድ 6 በዓምድ 3 ይሞላል፡፡

ጥያቄ 9 - በጥናቱ ዓመት ድርጅቱ ድረ-ገጽ (website) የነበረው/ያልነበረው መሆኑን ተጠይቆ ከነበረው ኮድ 1 ካልነበረው ደግሞ ኮድ 2 በዓምድ 3 ይሞላል፡፡

ጥያቄ 10 - የጥያቄ 9 መልሱ አዎን (ኮድ 1) ከሆነ ድርጅቱ ድረ-ገጹን (website) በአብዛኛው ለምን እንደተጠቀመው ተጠይቆ የድርጅቱን ምርትና ዋጋ ዝርዝር ለማሳወቅ ከሆነ ኮድ 1 የግዥ ትዕዛዝ ስመቀበል ከሆነ ኮድ 2 የግዥ ትዕዛዝ ስመስጠት (ግዥ ስመፈጸም) ከሆነ ኮድ 3 የአካባቢውን ባህል/ቋንቋ ለማስተማር ከሆነ ኮድ 4 ከላይ ከተጠቀሱት የተለዩ መረጃዎችን ለደንበኞች ለማቅረብ ከሆነ ኮድ 5 ድረ-ገጹን (website) ለምንም ያልተጠቀመበት ከሆነ ኮድ 6 በዓምድ 3 ይሞላል፡፡

ጥያቄ 11 - ድርጅቱ የICT (Computer, internet እና website) ተገልጋይ በመሆኑ መጠቀም አስመጠቀሙ ተጠይቆ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ኮድ 2 በዓምዱ 3 ይሞላል፡፡

## ክፍል 10 - አስተያየት

በዚህ ክፍል መረጃ ሰጪው በመጠይቁ ላይ ስለተካተቱት ጥያቄዎችም ሆነ በሌላ ተያያዥ ጉዳይ ላይ አስተያየት ካለው የሚገለጽበት ቦታ ነው።

## ክፍል 11 - ለተሰጠው መረጃ ጥያቄ ቢኖር መልስ ሊሰጥ የሚችል ሰው

በዚህ ክፍል በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ሥራው በቀጥታ የሚመለከተው ባለሥልጣን ወይም ወኪል ስለ ሥራው ትክክለኛነትና ማናቸውም የተሞላውን መረጃ በሚመለከት ጥያቄ ቢኖር በስልክ ጭምር መልስ ማግኘት ይቻል ዘንድ ስሙን፣ የሥራ ማዕረጉን፣ ስልክ ቁጥሩን በመሙላትና **በመፈረም የድርጅቱን ማህተም ማድረግ** ያስፈልጋል።

## ክፍል 12 - የመረጃ ሰብሳቢውና የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ

በመጨረሻም በዚህ ክፍል የባለሥልጣኑ መ/ቤት መረጃ ሰብሳቢና ተቆጣጣሪ እንዲሁም የመ/ቤቱ የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ሥራው በትክክል ለመከናወኑ ፊርማቸውንና ሥራው ያለቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመሙላት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

# የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ዓመታዊ ጥናት የተሞሉ መጠይቆችን የማመሳከሪያ ዘዴዎች፣

በአጠቃላይ የመጠይቁ የተለያዩ ክፍሎች/ዓምዶች እርስ በራሱ በማይጋጭ መንገድ ተገናዝበው በሚገባ የተሞሉ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ከዚህ በታች በዝርዝር የቀረቡትን የማመሳከሪያ ዘዴዎች በመከተል መረጃ ሰብሳቢውና ተቆጣጣሪው የተሞላውን መጠይቅ እንደገና መመርመር ያስፈልጋቸዋል።

1/ አንድ መረጃ ሰብሳቢ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን መጠይቅ ሞልቶ እንደጨረሰ ለመረጃ ተቆጣጣሪው ከማስረከቡ በፊት የመጠይቁ ክፍሎች በሙሉ መሞላታቸውንና መጠይቁ የሚሞላለት ፋብሪካ የማይመለከተው ክፍሎች ካሉ ክፍሉን በሚመለከት ጥያቄ መቅረቡን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ሠረዝ በማድረግ መታለፍ ይኖርበታል።

2/ በንዑስ ክፍል 3.1 ላይ ካሉት አራት ወራት በየትኛውም ወር በሁለቱም ፆታ የሰው ኃይል ቁጥር ከተሞላ በክፍል 3.2 ዓምድ 3 እና 4 ላይ ደመወዝ በሁለቱም ፆታ መሞላት ይኖርበታል። በተመሳሳይ ሁኔታ የውጭ ዜጋ በሚለው በንዑስ ክፍል 3.1 የሠራተኛ ቁጥር ከተሞላ በንዑስ ክፍል 3.2 ዓምድ 5 ላይ የተከፈለ የደመወዝ መጠን መሞላት ይኖርበታል።

3/ በንዑስ ክፍል 3.1 ሰዎች በወራት በቀጥታ በጥናቱ ዓመት የነበሩ የጊዜያዊ ሠራተኞች ቁጥር አለመሆኑን (የነበሩት ሠራተኞች ቁጥር ሲባዛ በሠሩበት ወራት መሆኑን) ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህንንም በበለጠ ለማረጋገጥ በዓምድ 16 የተሞላውን የምንዳ መጠን በዓምድ 15 ለተሞላው ሰዎች በወራት ቁጥር በማካፈል ለአንድ ጊዜያዊ ሠራተኛ በወር ሊከፈለው ከሚገባው በታች ወይም በላይ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

4/ በጥናት ዓመቱ ውስጥ ቅንስናሽ ሳይደረግ የተከፈለው ጠቅላላ የደመወዝ መጠን በአማካይ ከነበረው የሰው ኃይል ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ለማወቅ የዓመቱን ደመወዝ ለነበረው አማካይ የሰው ኃይል አካፍሎ ማየት ያስፈልጋል። በተመሳሳይ መንገድ በፆታ ለያይቶ በማካፈል ጭምር ማየት ተገቢ ነው። በዚህ መንገድ የሚገኙት ውጤቶች የትርፍ ጊዜ ክፍያን ግምት ውስጥ በማስገባት ሊታሰብ ከሚችለው በላይ ወይም በታች አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርብናል። አንዳንድ ጊዜ የተወሰኑ ፋብሪካዎች የጊዜያዊ ሠራተኞች ደመወዝን በክፍል 3.2 ደግመው ሊያስመዘግቡን ስለሚችሉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

5/ በክፍል 3.2 ዓምድ 9 ውስጥ የተሞላው ቁጥር የመንግሥት ፋብሪካ ከሆነ የጠቅላላ ደመወዝን 6 መቶኛ (የትርፍ ጊዜ ክፍያ ተቀንሶ) መብለጥ ወይም እኩል መሆን አለበት:: አብዛኛውን ጊዜ ግን ዓምዱ የሕይወት ኢንሹራንስን ስለሚጨምር የበለጠ እንደሚሆን ይጠበቃል::

6/ በ 3.3 የቋሚና ኮንትራት ሠራተኞች ብዛት በሚያገኙት ደመወዝ መጠን ተመድበው የሚገኘው ጠቅላላ የሰው ኃይል ቁጥር በ3.1 ዓምድ 12፣13 ና 14 ተራ ቁጥር 3 እና 4 ከሚገኘው አጠቃላይ ድምር (በሰኔ ወር በተራ ቁጥር 3 ና 4 ከተሰጠው የሰው ኃይል ቁጥር) ጋር እኩል መሆን ይገባዋል::

7/ በክፍል 4.1 ላይ የተሞላው የጠቅላላ የምርትና ሽያጭ ዋጋ በሽያጭ ላይ የሚከፈሉ ልዩ ልዩ ታክሶችን መጨመሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል:: በትርፍና ኪሣራ መግለጫዎች ላይ የሚገለጸው የሽያጭ መጠን በአብዛኛው የሽያጭ ታክሶችን ሳይጨምር ስለሚሆን በመጠይቁ ላይ የሚሞላው ጠቅላላ (Gross Sales) ሽያጭ የበለጠ መሆን ይገባዋል::

8/ በክፍል 4.1 ላይ የምርት መጠንና ዋጋ ከሽያጭ መጠንና ዋጋ ጋር እኩል ወይም የሚለያይበት ሁኔታዎች ስለሚያጋጥም በሚከተለው ሁኔታ ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሀ. በጥናት ዓመቱ የተመረተው ምርትና በተጨማሪም ከክምችት (Stock) ከተሸጠ የምርት መጠንና ዋጋ ከሽያጭ መጠንና ዋጋ ማነስ ይኖርበታል::

ለ. በጥናት ዓመቱ ከተመረተው ምርት ከፊሉ ብቻ ከተሸጠ የምርት መጠንና ዋጋ ከሽያጭ መጠንና ዋጋ መብለጥ ይኖርበታል::

ሐ. በጥናት ዓመቱ የተመረተው ምርት ብቻ ከተሸጠ (ከክምችት ካልተሸጠ) የምርት መጠንና ዋጋ ከሽያጭ መጠንና ዋጋ ጋር እኩል መሆን አለበት::

በተጨማሪም የምርት ዋጋንም ሆነ የምርት ሽያጭን በየእንዛራቸው ለተሞላው ብዛት (መጠን) በማካፈል የሚገኘው የአንዱ ዕቃ መካከለኛ ዋጋ በንዑስ ክፍል 4.1 ዓምድ 6 ከተሞላው ዋጋ ጋር ተቀራራቢ መሆኑን ማየት ተገቢ ነው:: የመጠን መለኪያን በሚመለከት ደግሞ በሜትሪክ መለኪያ (በተያያዘው ዝርዝር መሠረት) መሞላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

13

9/ በክፍል 4.1 ዓምድ 12 የተሞላው በጥናት ዓመቱ ሊመረት የሚችለው ጠቅላላ ዋጋ በዚሁ ክፍል 4.1 ዓምድ 8 ከተሞላው ጠቅላላ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እኩል ሊሆን ወይም ሊበልጥ ይችላል እንጂ ሊያንስ ስለማይችል ይህንኑ ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡

10/ በክፍል 4.3 ምንም ለውጥ ሳይደረግባቸው በተገዙበት ሁኔታ ተመልሰው ከተሸጡ ዕቃዎች (ዓምድ 4) የተገኘ ገቢ ከተመዘገበ በክፍል 6.2 በተገዙበት ሁኔታ ለተሸጡ ዕቃዎች የተደረገ ወጪ (ዓምድ 11) ቢያንስም ቢበዛም ወጪ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

11/ በክፍል 5 የተሞላው የክምችት ዋጋ ዝርዝር በሂሣብ ሪፖርት ላይ ከተመለከተው ጋር እኩል ወይም ተቀራራቢ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

12/ የጥሬ ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ ለመጠኑ ተካፍሎ የሚገኘው የአንዱ ዕቃ መካከለኛ ዋጋ ሊገመት ከሚችለው በላይ አለመሆኑን ማየትና ከአገር ውስጥ ሲደመር ከውጭ አገር ጠቅላላ ድምርን መስጠት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ወደ ታችና ወደ ጎን በመደመር የጠቅላላ ድምር ስህተት ካለ ከተስተካከለ በኋላ በሂሣብ ሪፖርት ላይ ካለው ቀጥተኛ የሆነ የጥሬ ዕቃ ወጭ (Direct raw material) እና ቀጥታ ያልሆነ የጥሬ ዕቃ ወጭ (Indirect raw material) ጋር እኩል (ተቀራራቢ) መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

13/ በክፍል 6.2 ዓምድ 6 ላይ የሚሞላው የነዳጅና የቅባት ወጭዎች ለፋብሪካው ሞተሮች ለኃይል ማመንጨትና ለቅባትነት የዋለውን እንጂ ለትራንስፖርት የዋለውን ነዳጅና ለኤሌክትሪክ ማመንጨት የዋለውን ነዳጅ ስለማይጨምር የተጋነነ ቁጥር ከተገኘ (በተለይ ከሲሚንቶ ከብርጭቆና ከሸክላ ፋብሪካዎች ውጪ ላሉ ድርጅቶች) የትራንስፖርት ሊሆን ስለሚችል እንደገና ተጠይቆ የትራንስፖርት ከሆነ በዚሁ ክፍል ንዑስ ክፍል 6.3 ዓምድ 6 ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

14/ በክፍል 6.3 ዓምድ 12 ሌሎች ወጪዎች ከጠቅላላ ወጪው ጋር ሲታይ የተጋነነ ከሆነ ዝርዝሩን እንደገና ጠይቀን ማስተካከል ይኖርብናል፡፡

15/ በምርት ሽያጭ ላይ የሚከፈሉ ልዩ ልዩ የሽያጭ ታክሶች በጣም ከተወሰኑ የምግብ ፋብሪካዎች በስተቀር በሁሉም የመንግሥትና የግል ፋብሪካዎች የሚሰበሰብ ስለሆነ ባዶ ሊሆን ስለማይችል ቢያንስ የተወሰነ ቁጥር መሞላቱን ማየት ይኖርብናል፡፡ ብዙዎቹ ፋብሪካዎች የሚከፍሉት አስራ አምስት በመቶ አካባቢ ሲሆን የመጠጥ ፋብሪካዎች ግን ኤክሳይዝ ታክስ ስለሚከፍሉ ከ30 እስከ 40 በመቶ ሊደርስ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

16/ በንዑስ ክፍል 7.1 ዓምድ 6 የሚሞላው የአገልግሎት ቅናሽ ድምር እጅግ ቢበዛ በዓምድ 3 ላይ ከቀረበው ከ20-25% በላይ ከሆነ የዓመቱ ሳይሆን የተጠራቀመ የአገልግሎት ቅናሽ (Accumulated Depreciation) ሊሆን ስለሚችል መረጃ ሰጪውን እንደገና በመጠየቅም ሆነ ከሂሣብ ሪፖርት ጋር በማስተያየት ማስተካከል ይኖርብናል።

17/ በንዑስ ክፍል 7.1 የዓምድ 3 ድምር፣ የዓምድ 6 ድምር፣ የዓምድ 7 ድምር ከሂሣብ ሪፖርቱ Beginning Net Book Value, Annual depreciation and Ending Net Book Value ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።

18/ በንዑስ ክፍል 7.1 ዓምድ 4 በዓመቱ ውስጥ ለመዋዕለ ንዋይ የወጣው ገንዘብ በንዑስ ክፍል 7.2 ዓምድ 3 ገንዘቡ በተገኘበት ምንጭ ከተዘረዘረው ድምር ጋር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

19/ በትርፍና ኪሣራ መግለጫ ላይ (የሂሣብ መዝገብ ላላቸው ብቻ) የምናገኘው ጠቅላላ የወጪ ድምርና ጠቅላላ የገቢ ድምር በመጠይቁ ላይ ከሞላነው ጋር እኩል ወይም በጣም ተቀራራቢ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

20/ በመጨረሻም በትርፍና ኪሣራ መግለጫው ላይ የሚገኘው ትርፍ (ኪሣራ) (Net surplus or loss before profit tax) በመጠይቁ ላይ ከተሞላው ጠቅላላ ገቢ ሲቀነስ ጠቅላላ ወጪ (ክምችትን ግምት ውስጥ በማስገባት) ጋር እኩል (በጣም ተቀራራቢ) መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

| የቋሚ ንብረቱ አገልግሎት ዘመን | የቋሚ ንብረት አገልግሎት ቅናሽ ማባዣ | | |
|---|---|---|---|
| | ኮምፒዩተርና ሶፍትዌር | ተሽከርካሪ፣ ማምረቻ መሣሪያና የቢሮ ዕቃች | ለሕንፃ |
| | 0.25 | 0.20 | 0.05 |
| 1 | 0.750 | 0.800 | 0.950 |
| 2 | 0.563 | 0.640 | 0.903 |
| 3 | 0.422 | 0.512 | 0.857 |
| 4 | 0.316 | 0.410 | 0.815 |
| 5 | 0.237 | 0.328 | 0.774 |
| 6 | 0.178 | 0.262 | 0.735 |
| 7 | 0.133 | 0.210 | 0.698 |
| 8 | 0.100 | 0.168 | 0.663 |
| 9 | 0.075 | 0.134 | 0.630 |
| 10 | 0.056 | 0.107 | 0.599 |
| 11 | 0.042 | 0.086 | 0.569 |
| 12 | 0.032 | 0.069 | 0.540 |
| 13 | 0.024 | 0.055 | 0.513 |
| 14 | 0.018 | 0.044 | 0.488 |
| 15 | 0.013 | 0.035 | 0.463 |
| 16 | 0.010 | 0.028 | 0.440 |
| 17 | 0.008 | 0.023 | 0.418 |
| 18 | 0.006 | 0.018 | 0.397 |
| 19 | 0.004 | 0.014 | 0.377 |
| 20 | 0.003 | 0.012 | 0.358 |
| 21 | 0.002 | 0.009 | 0.341 |
| 22 | 0.002 | 0.007 | 0.324 |
| 23 | 0.001 | 0.006 | 0.307 |
| 24 | 0.001 | 0.005 | 0.292 |
| 25 | 0.001 | 0.004 | 0.277 |
| 26 | 0.001 | 0.003 | 0.264 |
| 27 | 0.000 | 0.002 | 0.250 |
| 28 | 0.000 | 0.002 | 0.238 |
| 29 | 0.000 | 0.002 | 0.226 |
| 30 | 0.000 | 0.001 | 0.215 |
| 31 | 0.000 | 0.001 | 0.204 |
| 32 | 0.000 | 0.001 | 0.194 |
| 33 | 0.000 | 0.001 | 0.184 |
| 34 | 0.000 | 0.001 | 0.175 |
| 35 | 0.000 | 0.000 | 0.166 |
| 36 | 0.000 | 0.000 | 0.158 |
| 37 | 0.000 | 0.000 | 0.150 |
| 38 | 0.000 | 0.000 | 0.142 |
| 39 | 0.000 | 0.000 | 0.135 |
| 40 | 0.000 | 0.000 | 0.129 |

**አባሪ፣**

የምርትና የጥሬ ዕቃ መስፈሪያ በሜትሪክ መለኪያ እንዴት መስጠት እንዳለበት የሚያሳይ ምሳሌ በዝርዝር፣

# የምርት ዓይነትና የመጠን መለኪያ ዝርዝር

| የምርት ዝርዝር | የምርት መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| ሥጋ (የበሬ፣ የበግ፣ የፍየል) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በጣሳ ከተሰጠ አንድ ጣሳ ሊይዝ የሚችለው መጠን በኪ.ግራም/በግራም መገለጽ አለበት:: |
| የአትክልት ሾርባ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| ምንቸት አብሽ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| ሽሮ ወጥ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| ቲማቲም ድልህ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| የብርቱካን ጭማቂ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| የብርቱካን ማርማላት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| ዘይት | ሊትር፣ ኪነግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቆርቆሮ/በጣሳ ከተሰጠ አንድ ቆርቆሮ/ጣሳ ሊይዝ የሚችለው የዘይት መጠን በሊትር፣ በኪ.ግራም ወይም በግራም መገለጽ አለበት:: |
| ፋጉሎ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ወተት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ቅቤ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፎርማጅ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ዱቄት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የእንስሳት መኖ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጋሌታ | ግራም፣ ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ዳቦ | ግራም፣ ኪ.ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቁጥር ከተሰጠ የአንድ ዳቦ አማካይ ክብደት መጠን ምን ያህል እንደሆነ በግራም ይገለጽ:: |
| ብስኩት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ኬክ | ግራም፣ ኪ.ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቁጥር ከተሰጠ የአንድ ቁራሽ ኬክ የክብደት መጠን ምን ያህል እንደሆነ በግራም ይገለጽ:: |
| ድፎ ኬክ (ቶርታ፣ የልደት፣ የሠርግ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቁጥር ከተሰጠ የአንድ ድፎ ኬክ ክብደት ምን ያህል እንደሆነ በኪ.ግራም ይገለጽ:: |
| ከረሜላ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ስኳር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሞላሰስ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፓስታና መኮረኒ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሻይ ቅጠል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ቅመም | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የተፈጨ ቡና | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |

| የምርት ዝርዝር | የምርት መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| አልኮል መጠን (ጂን፣ ኡዞ፣ ኮኛክ፣ ቢተር ... ወዘተ) | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | -በጠርሙስ ከተሰጠ የአንድ ጠርሙስ ይዘት ምን ያህል ሲነሲ/ሊትር እንደሚይዝይገለጽ:: |
| አልኮል (ንፁህ አልኮል፣ እሳት አልኮል) | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | » » » |
| ወይን ና ቪኖ፣ ሳሪስ፣ ሻምፓኝ፣ ጉደር ... ወዘተ) | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | » » » |
| ቢራ ወይም ድራፍት | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | » » » |
| ብቅል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | » » » |
| የለስላሳ መጠጥ | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | » » » |
| የማዕድን ውኃ (አምቦ ውሃ ባቢሌ፣ ጠሳ፣ ቡሬ) | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | » » » |
| ሲጋራ | በሺህ ቁጥር | |
| የናይለን ጨርቅ | ካሬ ሜትር፣ በሺህ ካሬ ሜትር | |
| የጥጥ ጨርቅ | ካሬ ሜትር፣ በሺህ ካሬ ሜትር | |
| ድር የአክሪሊክ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ድርና ማግ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የሱፍ ብርድ ልብስ | ካሬ ሜትር፣ በሺህ ካሬ ሜትር | |
| የጥጥ ብርድ ልብስ | ቁጥር፣ በሺህ ቁጥር | |
| ቃጫና የቃጫ ገመድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የሱፍ ጨርቅ | ካሬ ሜትር | |
| የወለል ምንጣፍ | ካሬ ሜትር | |
| ጆንያ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ብትን ጆንያ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ክር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የተዳመጠ ጥጥ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሹራብ | ደርዘን፣ ቁጥር | |
| የውስጥ ልብስ (ካኒቴራ፣ የሌት ውስጥ ልብስ፣ ፓንት፣ ካልሲ፣ ስቶኪንግ) | ደርዘን | |
| ሸሚዝ | ደርዘን፣ ቁጥር | |
| አንሶላ | ጥንድ | |

| የምርት ዝርዝር | የምርት መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| ሌሎች ልብሶች (ኮት፣ ሱሪ፣ ጃኬት፣ ቁታ፣ የሥራ ካፖርት፣ የህፃን ልብስ፣ ባርኔጣ ...ወዘተ) | ደርዘን፣ ቁጥር | |
| የቆዳ ልብስ (የቆዳ ጃኬት፣ ሱሪ፣ ቀሚስ ...ወዘተ) | ደርዘን ፣ በቁጥር | |
| ጃንጥላ | ቁጥር | |
| የቆዳ ገበር | ስኩዌር ፊት፣ ስኩዌር ሜትር | |
| ብትን የልብስ ቆዳ | ስኩዌር ፊት | |
| በከፊል የተለፋ ቆዳ (የፍየልና የበግ) | ቁጥር፣ በሺህ ቁጥር | |
| በከፊል የተለፋ የበሬ ቆዳ | ስኩዌር ፊት | |
| የቆዳ ሶል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የፕላስቲክ ሶል | ጥንድ | |
| ሸራና ቦት ጫማ | ጥንድ | |
| የቆዳ ጫማ | ጥንድ | |
| የፕላስቲክ ጫማ | ጥንድ | |
| ኮምፔንሳቶ | ሜትር ኩዩብ | -በቁጥር ከተሰጠ የአንዱ ውፍረት መገለጽ አለበት |
| ቺፕ ውድ | ሜትር ኩዩብ | » » » |
| ፋይዚት | ሜትር ኩዩብ | » » » |
| ጣውላ | ሜትር ኩዩብ | |
| ሞራሌ | ቁጥር | |
| ሸሪራ | ቁጥር | |
| ወረቀት (ወረቀት፣ ሶፍት፣ ናፕኪን፣ ሌዲስታይል) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቁጥር ከተሰጠ የእያንዳንዱ ዕቃ ክብደት ምን ያህል እንደሆነ በኪሎ ግራም ይገለጽ:: |
| ካርቶን፣ የኪስ ወረቀት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ደብተር | ደርዘን፣ ቁጥር | |
| ኦክሲጂን | ሜትር ኪዩብ | |

| የምርት ዝርዝር | የምርት መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| አሲቲሊን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሴይክስ | ቁጥር፣ ኪሎ ግራም | –ቢቻል በኪሎ ግራም ይገለጽ:: |
| ቀለም | ሊትር፣ ኪሎ ግራም | |
| ሬዚን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ቫርኒሽና ላከር | ሊትር፣ ኪሎ ግራም | |
| ማጣበቂያ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ካፕሱል | ቁጥር፣ በሺህ ቁጥር | |
| ኢንጀክሽን 100ሴ | ቁጥር፣ በሺህ ቁጥር | |
| ሹሮፕ | ሊትር፣ በሺህ ሊትር | |
| እንክብል | በሺህ ቁጥር | |
| ቅባት መድኃኒት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፀረ-ሕዋሳት | በሺህ ቁጥር | |
| ሣሙና | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ቫዝሊን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | –በደርዘን ከተሰጠ በኪ.ግራም ይገለጽ:: |
| ፓራፊን /ፈሳሽ ቅባት/ | ሊትር፣ ኪሎ ግራም | –በጠርሙስ ከተሰጠ የ1 ጠርሙስ ይዘት በሊትር ይገለጽ:: |
| ሌሎች ቅባቶች | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | –በጠርሙስ ወይም በተለያዩ ዕቃዎች ቢሰጥም ጠቅላላ ይዘቱ በኪ. ግራም /በሊትር ይገለጽ:: |
| ሻማ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | –በካርቶን/ደርዘን ከተሰጠ የአንድ ካርቶን/ ደርዘን ክብደት በኪ.ግራም ይገለጽ:: |
| ሰም | ኪሎ ግራም | –በጣሳ ከተሰጠ የአንድ ጣሳ ሰም ክብደት በኪ. ግራም ይገለጽ:: |
| ጎማ | ቁጥር | –በኪ. ግራም ከተሰጠ በቁጥር ይለወጥ:: |
| ከመነዳሪ | ቁጥር | |
| የታደሰ ጎማ | ቁጥር | |
| ፕላስቲክ ክሬት (የለስላሣና የቢራና የአምቦ ውኃ ሣጥን) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የመብራት ገመድ | ሜትር፣ በሺህ ሜትር | |
| ካርቦን ዳይኦክሳይድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አስክሪብቶ | ቁጥር፣ በሺህ ቁጥር | |
| የፖሊቲሊን ውጤት (የፕላስቲክ ሣህን፣ ገመድ፣ ጆግ፣ የወለል ምንጣፍ፣ ስፖንጅ፣ ጆሪካን) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | –በቁጥር፣ በሜትር ኪዩብ ከተሰጠ ወደ ኪሎ ግራም ተቀይሮ መሞላት አለበት:: |
| ብርጭቆ | ቁጥር | |
| ጠርሙስ | ቁጥር | |

| የምርት ዝርዝር | የምርት መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| የሸክላ ጡብ | ቁጥር | |
| ጀሶ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጠመኔ | ግሮስ | |
| ኖራ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሲሚንቶ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ብሎኬትና ቱቦ | ቁጥር፣ በሺህ ቁጥር | |
| ከሲሚንቶ የተሠራ ታይል | ካሬ ሜትር | |
| እምነ በረድ | ሜትር ኪዩብ | |
| አስቤስቶስ | ቁጥር | |
| የቤት ክዳን ቆርቆሮ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የብረት ቱቦ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የማዕዘን ብረት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የአርማታ ብረት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሚስማር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሽቦ (የአልጋ፣ የአጥር፣ ወዘተ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የብረት በር | ካሬ ሜትር | –በቁጥር ከተሰጠ ወደ ካሬ ሜትር ይለወጥ |
| የብረት መስኮት | ካሬ ሜትር | » » » » |
| የመኪና ካሶኒ (ቦቴ፣ ታንከር፣የመኪና አካል) | ኪዩቢክ ሜትር | |
| የኤሌክትሪክ ምጣድ | ቁጥር | |
| ቆርኪ | ግሮስ | |
| ጣሳ | ቁጥር | |
| ባሌስትራ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የመኪና ባትሪ | ቁጥር | |
| አውቶቢስ | ቁጥር | |
| የጭነት መኪና | ቁጥር | |
| ተጎታች/ተሳቢ | ቁጥር | |
| ትራክተር | ቁጥር | |

| የምርት ዝርዝር | የምርት መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| የእንጨት በር | ካሬ ሜትር | -በቁጥር ከተሰጠ ወደ ካሬ ሜትር ይለወጥ:: |
| የእንጨት መስኮት | ካሬ ሜትር | » » » » |
| ቁምሣጥን | ቁጥር | |
| አልጋ | ቁጥር | |
| ቢፌ | ቁጥር | |
| ሶፋ | ሴት፣ ቁጥር | |
| ወንበርና ጠረጴዛ | ሴት፣ ቁጥር | -በሴት ከተሰጠ የወንበሩ ብዛት ስንት እንደሆነ ይገለጽ:: |

## የጥሬ ዕቃ ዓይነትና የመጠን መለኪያ ዝርዝር

| የጥሬ ዕቃ ዝርዝር | የጥሬ ዕቃ መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| ሥጋ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ከብት | ቁጥር | |
| ዘይት | ሊትር፣ ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -የቆርቆሮ/ጣሳ ዘይት ከሆነ የቆርቆሮው/ጣሳው ይዘት/ክብደት መጠን በሊትር/በኪ.ግራም ይገለጽ |
| አትክልት (ሽንኩርት፣ ድንች፣ ካሮት፣ ቲማቲም ... ወዘተ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥራጥሬ (አተር፣ ባቄላ፣ አደንጓሬ ...ወዘተ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ ብርቱካን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የብርቱካን ጭማቂ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በጣሳ ከተሰጠ የአንድ ጣሳ የክብደት መጠን ምን ያህል እንደሆነ መገለጽ አለበት፡፡ |
| የቅባት እህል (ተልባ፣ ኑግ፣ ጎመን ዘር፣ ሰሊጥ፣ ጥፍ ጥሬ ... ወዘተ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ ወተት | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | |
| ዱቄት ወተት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ ስንዴ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ በቆሎ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ዱቄት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ስኳር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጨው | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| እርሾ | ግራም፣ ኪ.ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቆርቆሮ/በፓኬት ... ከተሰጠ የአንዱ እሽግ እርሾ ክብደት በግራም/በኪ.ግራም ይገለጽ |
| ቅቤ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቆርቆሮ ከተሰጠ የአንድ ቆርቆሮ ቅቤ ክብደቱ በኪ.ግራም መገለጽ ይኖርበታል፡፡ |
| ሽንኮራ አገዳ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ግሉኮስ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አረንጓዴ ሻይ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ዛላ በርበሬ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ ቡና | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አልኮል | ሊትር፣ ሄክቶ ሊትር | |
| ሞላሰስ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |

| የጥሬ ዕቃ ዝርዝር | የጥሬ ዕቃ መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| ኢስንሶ | ሊትር፣ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ዘቢብ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የሎሚ ጭማቂ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጌሾ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ብቅል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጉብስ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ካርቦን ዳይኦክሳይድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የትምባሆ ቅጠል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ድር የአክሪሊክ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ማቅለምያ ቀለምና ኬሚካል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የጥጥ ልቃሚ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የተዳመጠ ጥጥ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የቃጫ ቅጠል | ሜትር ኪዩብ | |
| ድር የጥጥ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጁት ድርና ማግ (የቃጫ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ ጥጥ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ውል ዌስት አየሱፍ ልቃሚ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አክሪሊክ ፋይበር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፖሊስተር ፋይበር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የናይለን ድር | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ብትን የልብስ ቆዳ | ስኩዌር ፊት፣ ስኩዌር ሜትር | |
| ጨርቅ (ናይለን፣ ፖሊስተር፣ ጥጥ... ወዘተ) | ሜትር፣ ሜትር ካሬ፣ በሺህ ሜትር | |
| ጥሬ የበሬ ቆዳ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ኬሚካል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ጥሬ የበግና የፍየል ቆዳ | ቁጥር | |
| የጫማ ገበር | ስኩዌር ፊት፣ ስኩዌር ሜትር | |
| ፒነቪነሲነ ለጫማ ሶል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ብትን ቆዳ ለጫማ | ስኩዌር ፊት፣ ስኩዌር ሜትር | |
| ፕላስቲክ ሶል | ጥንድ | |
| የቆዳ ሶል | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ኅማ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የጫማ ማጣበቂያ ማስቲሽ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ግንድ | ሜትር ኩዩብ | |
| ቪነር | ካሬ ሜትር | |

| የጥሬ ዕቃ ዝርዝር | የጥሬ ዕቃ መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| ኮላ | ኪሎ ግራም | |
| ፐልፕ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ቆሻሻ ወረቀት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ኬሚካል (ቀለም ወዘተ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| የካርቶን መሥሪያ ወረቀት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ወረቀት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በሪም ከተሰጠ የአንድ ሪም ክብደት በኪሎ ግራም ምን ያህል እንደሆነ ይገለጽ። |
| ኮስቲክ ሶዳ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፓራፊን ዋክስ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሬዚን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፒግመንት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሞራ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሶዲየም ኮምፓውንድ (ጨው ...ወዘተ) | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፋቲ አሲድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፔትሮሊየም ጄሊ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፓራፊን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ስፌፍ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፒነሽነሲነ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፖሊቲሊን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ኩላንት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሲልካ ሳንድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አፈር (ነጭ፣ ቀይ) | ሜትር ኪዩብ | |
| ጂብሰም | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ኖራ ድንጋይ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፑምቼ | ሜትር ኪዩብ | |
| ሶዳ አሽ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| እምነበረድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ሲሚንቶ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አሸዋ | ሜትር ኪዩብ | -በመኪና የተሰጠ ከሆነ ወደ ሜትር ኪዩብ መለወጥ አለበት |
| ጠጠር | ሜትር ኪዩብ | » » » |
| የእምነበረድ ቋጥኝ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል | -በሜትር ኪዩብ ከተሰጠ የአንድ ሜትር ኪዩብ ክብደት በኪሎ ግራም መገለጽ አለበት |

| የጥሬ ዕቃ ዝርዝር | የጥሬ ዕቃ መጠን መለኪያ | አ ስ ተ ያ የ ት |
|---|---|---|
| ላሜራ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | -በቁጥር ከተሰጠ የአንድ ላሜራ ክብደት ይገለጽ |
| ጋልቨናይዝድ ኮይልስ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አሉሙኒየም | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| አይረን ቢሌት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ዋየር ሮድ | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ስብርባሪ ብረት | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ፒግ አይረን | ኪሎ ግራም፣ ኩንታል፣ ቶን | |
| ኤል. ቲ. ዜድ ብረት | ቁጥር፣ ሜትር፣ ኪ. ግራም፣ ኩንታል | |
| ክራውን ቲን ጨሌት | ሺት፣ በሺ.ህ ሺት | |
| የባትሪ ኬሚካል | ኪ. ግራም፣ ኩንታል፣ ሊትር | |
| ጣውላ | ኪዩቢክ ሜትር | |
| ኮምፔንሣቶ | ቁጥር | |
| ቺፐውድ | ቁጥር | |
| ፋይዚት | ቁጥር | |
| ፎርማይካ | ቁጥር | |
| ቫርኒሽ | ኪሎ ግራም፣ ሊትር | |

ለኢንዴክስ ማዘጋጃ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ምርቶች

## /መለኪያዎቹን በምርትና ጥሬ ዕቃ መለኪያ ላይ ይመልከቱ/

### የምግብ ምርቶች

የአትክልት ሾርባ
የበሬ የበግና የፍየል ሥጋ
ምንቸት አብሽ
ቲማቲም ድልህ
የብርቱካን መልማላት
የእንስሳት መኖ
ታሎው
የምግብ ዘይት
ፋጉሎ
ወተት
የስንዴ ዱቄት
ክሩቼሎ
ፋፋ
ዱቤ
ዕድገት
ፋሚክስ
የእንስሳት መኖ
የዶሮ ምግብ
ዳቦ
ኬክ
ብስኩትና ኩኪስ
ጋሌጣ
እንጀራ
ከረሜላ
ስኳር
ሞላሰስ
ፓስታና መኮሮኒ
ሻይ ቅጠል
የተፈጨ ቡና
ፓፕሪክ

### የመጠጥ ምርቶች

ጂን፣ ኡዞ፣ ኮኛክ፣ ቢተር
ንፁህ አልኮል፣ እሳት አልኮል
ወይን
ብቅል
ቢራ ወይም ድራፍት
የለስላሳ መጠጥ
የማዕድን ውሃ

### የሲጋራ ምርት

ሲጋራ

### የጨርቃ ጨርቅ ምርቶች

የአክሪሊክ ድር/ማግ
የተዳመጠ ጥጥ
የጥጥ ብርድ ልብስ
የሱፍ ብርድ ልብስ
ምንጣፍ
የጥጥ ፍሬ
የጥጥ ድርና ማግ
የስፌት ክር
የጥጥ ጨርቅ
የአልጋ ልብስ
ብትን ጆንያ
ሲባጎና ገመድ
የተዳመጠ ቃጫ
ጆንያ
ሹራብ
የውስጥ ልብስ
ሸሚዝ
ኮትና ሱሪ
ዣንጥላ

## የቆዳ ምርቶች

ያላለቀለት የበሬ ቆዳ

ያላለቀለት የፍየል ቆዳ

ገበር/ክበግ ቆዳ

ያላለቀለት የበግ ቆዳ

የጫማ ሽፋን

ክረስት ሺ.ፕ

የቆዳ ጫማ

የፕላስቲክና የጫማ ማስሪያ

የፕላስቲክ የጫማ ሶል

## የእንጨት ምርቶች

ቲምበር

ፕላይወድ

ፓርቲክል ቦርድ

## ወረቀትና የወረቀት ምርቶች

ደብተር

ወረቀት

የሽንት ቤት ወረቀት

ናፕኪን

## የኬሚካል ምርቶች

ሴዲክስ

አስትሊን

ኦክስጅን

ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ

ማጣበቂያ /ማስቲሽ/

ቨርኒሀ ላከር

ቀለም

ኢንጀክሽን 100A

ታብሌት

ካፕሱል

ሽሮፕ

ፀረ-ሕዋሳት /አንቲባዮቲክ/

ኦአር ኤስ

አይቪ ፍሉድ

ቅባት

ፓራፊን

ሳሙና

ሻማ

የወለል ሰም

ባትሪ ድንጋይ

የታደሰ ጎማ

ጎማ

ቱቦ

ፎም

ፕላስቲክ ክሬት /የለስላሳ እና የቢራ ሳጥን/

የመብራት ገመድ

የፕላስቲክ መያዣ

እስክሪፕቶ

የፖሊትሊን ውጤቶች

የፕላስቲክ ቱቦ

## ብረት ነክ ያልሆኑ ምርቶች

ብርጭቆ

ጠርሙስ /የብርጭቆ/

የሸክላ ጡብ

ሲሚንቶ

ኖራና ጀሶ

ቾክ

ከሲሚንቶ የተሰራ ጡብ (HCB)

የወለል ሸክላ

ከሲሚንቶ የተሰራ ጡብ

እምነበረድ

ጠጠር

የኖራ ድንጋይ

## የብረታ ብረት ምርቶች

አይረን በር
አይረን ሽት
ቤድ ስፕሪንግ ኔት
ሽቦ
የቤት ክዳን ቆርቆሮ
ስትራክቸራል ቱቦ
ወተር ፒፕ
የብረት በር
መጥበሻ
ማንቆርቆሪያ
ሰስፖ
ማጠቢያ ገንዳ
አካፋ
መጥረቢያ
ዲጅኖ
መዶሻ
ማጭድ
ሞልድ
ቆርኪ
ጣሳ
ባሌስትራ
ሚስማር
የኤሌክትሪክ ምጣድ
ክብደት መለኪያ ማሽን
ቋት
የመኪና ባትሪ
የመኪና አካል
አውቶብስና የጭነት መኪና
ተጎታች/ተሳቢ
ትራክተር
ሳይክል

## የቤትና የቢሮ ዕቃ ማምረቻ ውጤቶች

ጣውላ /ፕላንክ/
ፕላይውድ
ፎርማይካ
ቺፕውድ
ቬነር